**መመሪያ ቁ. 35/2013**

**የንግድ የመንገድ የጭነት ትራንስፖርት ኦፕሬተር አደረጃጀት፣ ብቃት ማረጋገጫና አፈጻጸም መመሪያ**

የፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን በአዋጅ ቁ.468/97 አንቀጽ 7 (2) መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “የንግድ የመንገድ የጭነት ትራንስፖርት ኦፕሬተር የአደረጃጀት ብቃት ማረጋገጫና የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 35 / 2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1. “አዋጅ” ማለት ትራንስፖርትን ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 468/1997 ነው፡፡
2. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሰጡት ትርጓሜዎች እንደአግባቡ ለዚህ መመሪያም ተፈጻሚዎች ይሆናሉ፡፡
3. “የጭነት ማመላለሻ ተሽከርካሪ” ማለት ማንኛውንም ዓይነት ዕቃ ወይም ጭነት እንዲያመላልስ ተብሎ የተሰራ ባለሞተር ተሽከርካሪ ነው፡፡
4. “አባል” ማለት በዚህ መመሪያ የተመለከቱትን መስፈርቶች በማሟላት በማኅበር ወይም በድርጅት የታቀፈ አባል ነው፡፡

**DIRECTIVE No.35 /2020**

**ORGANIZATIONAL STRUCTURE AND COMPETENCY OF COMMERCIAL ROAD FREIGHT TRANSPORT OPERATORS IMPLEMENTATION DIRECTIVE**

This Directive is issued by the Federal Transport Authority in accordance with Article 7 /2/ of Proclamation No. 468/2005.

## Part One

## General Provisions

### 1. Short Title

This Directive may be cited as “Organizational structure and competency of commercial road freight transport operators’ implementation directive No. 35 /2020”.

### 2. Definition

In this Directive, unless the context requires otherwise, words shall have the following meanings.

1/ “Proclamation” means Transport Proclamation No. 468/2005.

2/ Definitions given under Article 2 of the Proclamation shall be applicable to this Directive where appropriate.

3/ “Freight Transport Vehicle” means any motorized vehicle designed for the transportation of any item or freight.

4/ “Member” means a member of an association or business organization that meets the requirements set forth in this directive.

5. “የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት” ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት በጭነት ማመላለሻ ንግድ ሥራ ለተሠማሩ ኦፕሬተሮች የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ነው፡፡
6. “ደረጃ” ማለት በጭነት ማመላለሻ ኦፕሬተርነት ተመዝግበው በዚህ መመሪያ በተዘጋጀው መሥፈርት መሠረት የሚሰጥ ደረጃ ነው፡፡
7. “ኦፕሬተር” ማለት በመንገድ ጭነት ማመላለሻ ንግድ ስራ በማኀበር ወይም በድርጅት ወይም በግል ትራንስፖርት በዚህ መመሪያ አንቀፅ 8 ተመዝግቦ የተሰማራ ነው፡፡
8. "ማኀበር" ማለት በጭነት ማመላለሻ ንግድ ስራ ላይ በተሰማሩ ሰዎችና ድርጅቶች የተቋቋመና በአዋጁ መሰረት የተመዘገበ ነው፡፡
9. ”ድርጅት” ማለት የጭነት ማመላለሻ ንግድ ስራ ለማከናወን በንግድ ህግ መሠረት የተቋቋመና በአዋጁ መሰረት የተመዘገበ ነው፡፡
10. “አደራጅ አካል” ማለት በአዋጅ ቁጥር 468/1997 የተቋቋመው የትራስፖርት ባለስልጣን ወይም ይህንን ተክቶ የሚቋቋም አካል ነው፡፡
11. “ስቲከር” ማለት ትራስፖርት ኦፕሬተሩን የሚገልፅ ሙሉ መረጃ የያዘና በተሽከርካሪዎች ላይ የሚለጠፍ መለያ ምልክት ነው፡፡
12. “የተቀናጀ የጭነት ትራንስፖርት ኦፕሬተር አስተዳደር ስርዓት” ማለት የኦፕሬተሮችን ዝርዝር፣ የምዝገባ እና የደረጃ አሰጣጥ ሁኔታ፣ የተሽከርካሪ እና የአሽከርካሪ ዝርዝር መረጃ ለመመዝገብ እና ለመቆጣጠር የሚያስችል የኤሌክትሮኒክስ ስርዓት ነው፡፡

5/ “Certificate of Competence” means a certificate issued to freight operators in accordance with this Directive in testimony to their competence.

6/ “Level” means a level assigned to freight operators registered in accordance with this Directive.

7/ “Operator” means a person, Company or association engaged in freight transport as per Article 8 of this Directive.

8/ “Association” means a body established by persons or business organizations engaged in freight transport; and registered in accordance with the Proclamation.

9/ “Company” means a business entity established in accordance with the Commercial Code with the objective of operating freight transport and registered as so as per the Proclamation.

10/ “Organizing Body” means the Federal Transport Authority established under Proclamation No. 468/2005 or an organ that may be replacing the Authority.

11/ “Sticker” means a distinguishing sign containing details of the Operator and to be stickered on the vehicles.

12/ “Integrated freight transport operator management system” means an electronics system which includes the list of operators, their Registration and level status, detail of vehicle and Driver.

## 3. ዓላማ

መመሪያው የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡

1. ግልፅና የጠራ የአደረጃጀት ሥርዓት በመዘርጋት በቴክኖሎጂ ውጤቶች የታገዘ ጠንካራና ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት የሚከተሉ የጭነት ትራንስፖርት ኦፕሬተሮችን ማፍራት፤
2. አዳዲስ ባለሃብቶች ወደ ዘርፉ የሚገቡበትን ሁኔታ በማመቻቸት የአገልግሎቱን ቀጣይነት ማረጋገጥ፤
3. በዘርፉ ከፍተኛ አቅምና ብቃት ያላቸውን ኦፕሬተሮችን በመፍጠር በመካከላቸው ያለውን ውድድር ከፍ ማድረግና የተቀናጀ የሎጂስቲክስ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት በመዘርጋት ጭነቶች/ዕቃዎች ጊዜና ወጪ ቆጣቢ በሆነ ሁኔታ እንዲጓጓዙ ማስቻል፣
4. የጭነት ስፔሻላይዜሽንን በማበረታታት ኦፕሬተሮች በተለያየ የጭነት ዓይነት ማጓጓዝ ላይ ተሰማርተው እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤
5. የሀገር ውስጥ ኦፕሬተሮች አሰራር፣ ብቃትና አደረጃጀት በአፍሪካ በሚኖረው ቀጠናዊ እና የሁለትዮሽ የትራንስፖርት ትስስር ውስጥ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሀገር አቋራጭ እና በአለምዓቀፍ የንግድ የመንገድ ጭነት ማመላለሻ ንግድ ሥራ ላይ በአደራጁ አካል የተደራጁና ፈቃድ የወሰዱ ኦፕሬተሮች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 3. Objectives

The objectives of the Directive are the following:

1/ To enable the establishment of Freight Transport Operators with a clear organizational system that employs technology supported data management system;

2/ To ensure the sustainability of the freight transport service by creating enabling situations to new entrants in to the service;

3/ To ensure a competitive and integrated working environment in the logistics services through creating able and equating operators with a view to enabling efficient freight transport;

4/ To create a conducive environment, through encouraging specialization, for freight transport operators to engage in specialized freight transports.

5/ The operation, efficiency and organization of local operator to make them competitive in the regional and bilateral transport links in Africa

## 4. Scope of Application

This Directive shall be applicable on Operators engaged in the business of cross country and international freight transport services; and established and registered by the Establishing Organs.

## ክፍል ሁለት
## የኦፕሬተሮች ተግባርና ኃላፊነት

### 5. የኦፕሬተሩ ተግባርና ኃላፊነት

በንግድ የመንገድ ጭነት ማመላለሻ አገልግሎት ላይ ኦፕሬተር ሆኖ ለመስራት የሚፈልግ ማንኛውም ኦፕሬተር፣

1. በአዋጁና በዚህ መመሪያ ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶችን በማሟላት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የመውሰድ፣
2. የተሟላ የሥራ ሬከርድና ሠነድ አሟልቶና አደራጅቶ የመያዝ፣
3. ሥራ አስኪያጅ ሲለቅ እና ሲቀጥር ለባለስልጣኑ የማሳወቅ፣
4. የመንገድ ትራፊክ ደኅንነት ዩኒት በማቋቋም አደጋን ለመቀነስ በሚደረገው ሀገራዊ ጥረት ተሣታፊ የመሆን፣
5. በባለሥልጣኑ መስሪያ ቤት የወጡ ደንቦችና ሕጐችን አክብሮ በተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መሰረት አገልግሎት የመስጠት፣
6. ያሉትን ተሽከርካሪዎች ዓይነትና ብዛት፣ የተሸፈነ ርቀት፣ የተጓጓዘ ጭነት ብዛት፣ የሰው ኃይልና የቢሮ አደረጃጀት ወቅታዊ የገበያ ዋጋ /ታሪፍ/ መረጃና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች በየወሩ ለአደራጁ አካል የመስጠት፣
7. ሌሎች በሞዴል መተዳደሪ ደንቡ የተዘረዘሩ ተግባራትን የመተግበር ግዴታ አለበት፡፡

## Part Two
## Duties and Responsibilities of Operators

### 5.Duties and Responsibilities of Operator

Any Operator intending to engage in commercial freight transport services shall:

1/ secure a Certificate of Competence meeting the requirements set forth under the Proclamation and this Directive;

2/ keep complete record of operations and documents;

3/ notify the Authority of the resignation or employment of the General Manager;

4/ establish a traffic safety unit and be part of the national road safety initiatives

5/ Observe the laws and regulations of the Authority and provide the services for which it is issue the Certificate of Competence;

6/ consolidate data as to the types and numbers of vehicles, trips covered, volume of freight transported, personnel and office structure, current market tariff and any other relevant information; and forward same to the Establishing Organs every month.

7/ Carry out other activities as stipulated in the Model Articles of Association.

## 6. በመንገድ የጭነት ማመላለሻ ስራ ስለመደራጀት

### 1. በማኅበር

ሀ/ በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀፅ (2) መሠረት ማህበር አቋቁመው የንግድ የመንገድ የጭነት ማመላለሻ አገልግሎት መስጠት የሚፈልጉ የትራንስፖርት ማህበራት በዚህ መመሪያ በተቀመጠው ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ አራት የጭነት ማመላለሻ ትራንስፖርት አገልግሎት ውስጥ በሚያሟሉት መስፈርት መሰረት መደራጀት ይችላሉ፡፡

ለ/ በአንድ ማኅበር ውስጥ ሊኖሩ የሚገባቸው የአባላት ብዛት ከ25 (ሃያ አምስት) ማነስ የለበትም፡፡

ሐ/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ-አንቀፅ 1(ለ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አደራጅ አካሉ ለማኅበሩ የሚሰጠው ደረጃ በአባላት ብዛት እና/ወይም በተሽከርካሪዎች ብዛት መሰረት ይወሰናል፡፡

መ/ የጭነት ትራንስፖርት ማህበራት ስም ስያሜ ማንኛውንም አይነት ብሔርን፣ ኃይማኖትን፣ ዘርን፣ ጾታን እና ፖለቲካን የማያንቋሽሽ መሆኑ በአደራጅ አካሉ ተረጋግጦ ስያሜው የሚፀድቅ ሲሆን በጭነት ትራንስፖርት ዘርፍ አንድ ተመሳሳይ የማህበር ስም ስያሜ ለሌላ ማህበር አይሰጠም፡፡

## 6. Organization in Road Freight Transport

### 1/ Association

a) Commercial freight transport operators intending to be organized as Association in accordance with the Proclamation and sub-article (2) of Article 8 of this Directive may be organized from level One to level four depending on the requirements which they meet as set out in this Directive.

b) The number of members to form an Association shall not be less than 25 /Twenty Five/.

c) Without prejudice to the provisions of sub-article 1(b) of this Article, the level to be assigned to an Association by the organizing body shall be determined based on the number of members and/or the number of vehicles;

d) Nomenclature of Freight Transport Associations may be endorsed by the organizing body only after confirmation that it doesn't demean any ethnic group, religion, nationality, sex or political outlook; and nomenclature assigned to one Association can't be assigned as the same time to other Association in the freight transport sector;

ሠ/ በማኅበር የተደራጁ ኦፕሬተሮች በአዋጁ አንቀጽ 15 መሠረት በህግ የተሰጣቸውን መብት እና ግዴታ ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያዘጋጁት መተዳደሪያ ደንብ በአደራጅ አካሉ መጽደቅ አለበት፡፡

2. በድርጅት

ሀ/ በአዋጁ እና በዚህ መመሪያ አንቀፅ 8 ንዑስ-አንቀፅ (3) መሠረት ድርጅት አቋቁመው የንግድ የመንገድ የጭነት ማመላለሻ አገልግሎት መስጠት የሚፈልጉ የትራንስፖርት ድርጅቶች በዚህ መመሪያ በተቀመጠው ከደረጃ አንድ እስከ አምስት ባሉት የጭነት ማመላለሻ ትራንስፖርት አገልግሎቶች ውስጥ በሚያሟሉት መስፈርት መሰረት መደራጀት ይችላሉ፡፡

ለ/ በድርጅት የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ ሰው ከሚመለከተው አካል የትራንስፖርት የንግድ ፈቃድ ማቅረብ ይኖርበታል፣

ሐ/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ-አንቀፅ (2)(ሀ) አደራጅ አካሉ ለድርጅቱ የሚሰጠው ደረጃ በተሽከርካሪዎች ብዛት መሰረት ይወሰናል፡፡

e) The Articles of Association of Operators organized in Association made up as per Article 15 of the Proclamation shall be endorsed by the Establishing Organ.

**2/ Company**

a) Commercial freight transport operators intending to be organized as a Company in accordance with the Proclamation and sub-article (3) of Article 8 of this Directive may be organized from level One to level five depending on the requirements which they meet as set out in this Directive.

b) A person intending to operate a freight transport as a Company shall secure a business license for transport from the appropriate organ.

c) The level to be assigned by the Establishing Organ to the Company in accordance to sub-article (2)(a) of this Article shall be determined based on the number of vehicles.

## ክፍል ሦስት

## የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ዓይነቶች እና የአደረጃጀት መሥፈርቶች

7. **የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ዓይነቶች**

1. በንግድ በመንገድ የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት ሥራ ላይ የሚሠማሩ ኦፕሬተሮች እንደሚያቀርቧቸው ተሽከርካሪዎች ሁኔታ እና እንደሚመርጡት የትራንስፖርት ዓይነት የሚገባቸው የኦኘሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ይሰጣቸዋል፡፡
2. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 8 በተቀመጠው የደረጃ መለያና መሥፈርት መሰረት የሚሰጠው የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ፡-

ሀ/ ደረጃ1 የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ፤
ለ/ ደረጃ2 የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ፤
ሐ/ ደረጃ3 የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ፤
መ/ ደረጃ4 የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ እና
ሠ/ ደረጃ5 የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ናቸው፡፡

8. **በየደረጃው መሟላት ያለባቸው የደረጃ መለያ መስፈርቶች**

1. **በሁሉም ኦፕሬተሮች እኩል መሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች**

ሀ. ድንበር ለሚሻገር ኦፕሬተር ከሀገር ውጪ ቢያንስ 1 ወኪል ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሊኖረው ይገባል፡፡

ለ. በሀገር ውስጥ ዋና መ/ቤት ያለው ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ ቅ/ፅቤት ሊከፍት ይችላል፣

## Part Three

## Types of operator competency and organizational Requirement

**7.Types of operator competency**

1/ Operators engaged in commercial road freight transport services shall be issue with an operator competency certificate depending on the condition of the vehicles and the type of transport they choose.

2/ The Operator competency Certificate issued in accordance with the standards and requirements set out in Article 8 of this Directive are:

a) Level 1 Operator competency License:
b) Level 2 Operator competency License:
c) Level 3 Operator competency License:
d) Level 4 Operator competency License and
e) Level 5 Operator competency License.

**8. Level identification Requirements to be met at each level**

1/ **Requirements needs to be met equally by all operators**

a) shall have at least one agent or branch office in a foreign country for international road transport operator.
b) shall have head office in the country and may open branch office as needed.

ሐ. ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ ወቅታዊ የተሽከርካሪ የቴክኒክ ምርመራ የምስክር ወረቀት እና የጭነት ኢንሹራንስ ማቅረብ አለበት፡፡

መ.ሁሉም ተሽከርካሪዎች አደራጅ አካሉ ባስቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት አገልግሎት የሚሰጥ የተቀናጀ የጂፒኤስ እና የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ የተገጠመላቸው መሆን አለባቸው፡፡

ሠ.ማህበሩ የተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር የሚረዳ ስርዓት በራሱም ሆነ በሶስተኛ ወገን የሚተዳደር የተሽከርካሪ መቆጣጠሪያ ስርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡

ረ. አደራጅ አካሉ የማህበሩን የተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ መረጃዎችን ለማግኘት በሚያስችለው መልኩ የተዘረጋውን ሰርዓት 24 ሰዓት ክፍት ማድረግ አለበት፡፡

ሰ.ጂፒኤስ እና የፍጥነት መገደቢያ መሳሪያ የተገጠመላቸው ተሽከርካሪዎችን ዝርዝር መረጃ የያዘ ማረጋገጫ ሰነድ ማቅረብ አለበት፡፡

ሸ. የራሱ ጥገና ጋራዥ ካለው ለዚህ ተቀባይነት ያለው የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ወይም ከሌለው ከታወቀ የጥገና ተቋም የጥገና አገልግሎት የሚያገኝበት ቢያንስ የአንድ ዓመት ህጋዊ ውል ማቅረብ አለበት፡፡

ቀ. ማህበር ከሆነ ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የተመደበ አሽከርካሪ ዝርዝር፣ ከባለንብረቱ ጋር የተፈፀመ የስራ ቅጥር ውልና የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ኦርጂናልና ኮፒ ማቅረብ አለበት፡፡

c) Each vehicle is required to provide a current vehicle technical inspection certificate and cargo insurance.

d) All vehicles must be equipped with an integrated GPS and speed limiter in accordance with the standards set by the organizing body.

e) must have a vehicle control system administered by its self or third party, which can help to control the movement of vehicles.

f) Shall open the vehicle movement information through the vehicle control system in such a way that the organizing body has access to it.

g) Present detailed verification documentation for vehicles equipped with integrated GPS and speed limiter.

h) Shall have its own repair garage or at least one-year legal contract of maintenance service from a reputable maintenance service organization.

i) The association must provide list of drivers assigned to each vehicle, an employment contract with the vehicle owner and an original and copy of the driver's license.

በ. ድርጅት ከሆነ ከአሽከርካሪዎች ጋር የተፈፀመ የስራ ቅጥር ውልና የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ኦርጂናልና ኮፒ ማቅረብ አለበት፣

ተ. ልዩ ጎታች ተሽከርካሪዎች የመጫን አቅማቸው በተጣመረው ተሳቢ የመጫን ልክ የሚወሰን ሲሆን በኪራይ ከሆነ ህጋዊ የኪራይ ውል መቅረብ ይኖርበታል፡

2. <u>የማህበራት የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ መስፈርት፣</u>

ሀ. <u>ደረጃ 1 የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት</u>

1. የአባላት ወይም የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት ቢያንስ 150 መሆን አለበት፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (2)(ሀ)(1) የተገለጸው የተሽከርካሪ እድሜ ከ15 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፣
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (2)(ሀ)2 የመጫን አቅም ከ 30 ቶን ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፣
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (2)(ሀ)1፣ (2)(ሀ)2 እና (2)(ሀ)3 የተገለጹት ተሽከርካሪዎች በአንድ ጊዜ ጭነት የማንሳት አቅማቸው 4500 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፣
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (2)(ሀ)1፣ (2)(ሀ)2 እና (2)(ሀ)3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጡ ተሽከርካሪዎችን እና ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ ተሽከርካሪዎችን በአባልነት ሊይዝ ይችላል፡፡

j) The company must provide the original and a copy of an employment contract with the drivers and driver's license.

k) The loading capacity of special truck tractor shall depend on the loading capacity of the combined trailer and if rented, a legal lease contract shall be provide.

2/ **<u>Operator competency requirement for Associations;</u>**

A. **<u>competency requirement for Level 1 operator</u>**

1/ The number of members or initial vehicles shall not be less than 150.

2/ The vehicles age specified under sub-article (2) (A) 1 of this Article shall not exceed 15 years.

3/ The loading capacity of the vehicle specified under sub-article (2) (A) 2 of this Article shall not be less than 30 tons.

4/ The vehicles referred to under sub-article (2) (A) 1, (2) (A) 2 and (2) (A) 3 of this Article shall be able to lift at least 4,500 tons at a time.

5/ If the requirements specified under sub-articles (2) (A) 1, (2) (A) 2 and (2) (A) 3 of this Article are met, it may hold other vehicles not older than 30 years of age and other vehicles with a load capacity of not less than 20 tons.

ለ. **<u>ደረጃ 2 የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት</u>**

1. የአባላት ወይም የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት ቢያንስ 100 መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (2)(ለ)(1) የተገለጸው የተሽከርካሪ እድሜ ከ15 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (2)(ለ)(2) የመጫን አቅም ከ 30 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)(ለ)1፣ (2)(ለ)2 እና (2)(ለ)3 የተገለጹት ተሽከርካሪዎች በአንድ ጊዜ ጭነት የማንሳት አቅማቸው ከ3000 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)(ለ)1፣ (2)(ለ)2 እና (2)(ለ)3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጠ ተሽከርካሪዎችን እና ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ ተሽከርካሪዎችን በአባልነት ሊይዝ ይችላል፡፡

**B. <u>competency requirement for Level 2 operator</u>**

1/ The number of members or initial vehicles shall not be less than 100.

2/ The vehicles age specified under sub-article (2) (B) 1 of this Article shall not exceed 15 years.

3/ The loading capacity of the vehicle specified under sub-article (2) (B) 2 of this Article shall not be less than 30 tons.

4/ The vehicles referred to under sub-article (2) (B) 1, (2) (B) 2 and (2) (B) 3 of this Article shall be able to lift at least 3,000 tons at a time.

5/ If the requirements specified under sub-articles (2) (B) 1, (2) (B) 2 and (2) (B) 3 of this Article are met, it may hold other vehicles not older than 30 years of age and other vehicles with a load capacity of not less than 20 tons.

**ሐ. <u>ደረጃ 3 የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት</u>**

1. የአባላት ወይም የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት ቢያንስ 75 መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)(ሐ)1 የተገለጸው የተሽከርካሪ እድሜ ከ15 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)(ሐ)2 የመጫን አቅም ከ 30 ቶን ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)(ሐ)1፣ (2)(ሐ)2 እና (2)(ሐ)3 የተገለጹት ተሽከርካሪዎች በአንድ ጊዜ የማንሳት አቅማቸው ከ2250 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፣
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)(ሐ)1፣ (2)(ሐ)2 እና (2)(ሐ)3 የተገለጹትን መስፈርተቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጠ ተሽከርካሪዎችን እና ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ ተሽከርካሪዎችን በአባልነት ሊይዝ ይችላል፡፡

**መ. <u>ደረጃ 4 (ሀገር ውስጥ) የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ መስፈርት</u>**

1. የአባላት ወይም የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት ቢያንስ 50 መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)(መ)1 የተገለጸው ተሽከርካሪ እድሜ ያልተገደበ ነው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)(መ)2 የተገለጸው ተሽከርካሪ የመጫን አቅም ከ 7 ቶን ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፡፡

**C. <u>Competency requirement for Level 3 operator</u>**

1/ The number of members or initial vehicles shall not be less than 75

2/ The vehicles age specified under sub-article (2) (C) 1 of this Article shall not exceed 15 years.

3/ The loading capacity of the vehicle specified under sub-article (2) (C) 2 of this Article shall not be less than 30 tons.

4/ The vehicles referred to under sub-article (2) (C) 1, (2) (C) 2 and (2) (C) 3 of this Article shall be able to lift at least 2,250 tons at a time.

5/ If the requirements specified under sub-articles (2) (C) 1, (2) (C) 2 and (2) (C) 3 of this Article are met, it may hold other vehicles not older than 30 years of age and other vehicles with a load capacity of not less than 20 tons.

**D. <u>Competency requirement for Level 4/ Cross country road transport / operator</u>**

1/ The number of members or initial vehicles shall not be less than 50.

2/ The vehicles age specified under sub article (2)(D)1 of this Article is unlimited.

3/ The loading capacity of the vehicle specified under sub-article (2) (D) 2 of this Article shall not be less than 7 tons.

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2)(መ)1፣ (2)(መ)2 እና (2)(መ)3 የተገለጹት ተሽከርካሪዎች በአንድ ጊዜ ጭነት የማንሳት አቅማቸው 350 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

3. **<u>የድርጅት የኦፐሬተር ብቃት ማረጋገጫ መስፈርት፣</u>**

1. **<u>ለአክሲዮን ማኅበር</u>**

ሀ. **<u>ደረጃ 1 የኦፐሬተር የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት</u>**

1. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት ቢያንስ 50 መሆን አለበት፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)1(ሀ)1 የተገለጸው የተሽከርካሪ እድሜ ከ15 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(1)(ሀ)2 የመጫን አቅም ከ 30 ቶን ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(1)(ሀ)1፣ (3)(1)(ሀ)2 እና (3)(1)(ሀ)3 የተገለጹትን ተሽከርካሪዎች በአንድ ጊዜ ጭነት የማንሳት አቅማቸው ከ1500 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፣
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(1)(ሀ)1፣ (3)(1)(ሀ)2 እና (3)(1)(ሀ)3 የተገለጹትን መስፈርተቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጠ ተሽከርካሪዎችን እና ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት ሊይዝ ይችላል፡፡

4/ The vehicles referred to under sub-article (2) (D) 1, (2) (D) 2 and (2) (D) 3 of this Article shall be able to lift at least 350 tons at a time.

3. **<u>Operator competency requirement for Enterprise</u>**

1/ **<u>For a Share company</u>**

A. **<u>competency requirement for Level 1 operator</u>**

1/ The number of initial vehicles shall not be less than 50

2/ The vehicles age specified under sub-article (3) (1) (A) 1 of this Article shall not exceed 15 years.

3/ The loading capacity of the vehicle specified under sub-article (3) (1) (A) 2 of this Article shall not be less than 30 tons.

4/ The vehicles referred to under sub-article (3) (1) (A) 1, (3) (1) (A) 2 and (3) (1) (A) 3 of this Article shall be able to lift at least 1,500 tons at a time

5/ If the requirements specified under sub-articles (3) (1) (A) 1, (3) (1) (A) 2 and (3) (1) (A) 3 of this Article are met, it may hold other vehicles not older than 30 years of age and other vehicles with a load capacity of not less than 20 tons.

ለ. **ደረጃ 2 የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት**

1. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት ቢያንስ 30 መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(1)(ለ)1 የተገለጸው የተሽከርካሪ እድሜ ከ15 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(1)(ለ)2 የመጫን አቅም ከ 30 ቶን ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(1)(ለ)1፣ (3)(1)(ለ)2 እና (3)(1)(ለ)3 የተገለጹትን ተሽከርካሪዎች በአንድ ጊዜ የማንሳት አቅማቸው ከ900 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፣
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(1)(ለ)1፣ (3)(1)(ለ)2 እና (3)(1)(ለ)3 የተገለጹትን መስፈርተቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጡ ተሽከርካሪዎችን እና ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት ሊይዝ ይችላል፡፡

ሐ. **ደረጃ3 የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት**

1. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት ቢያንስ 20 መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(1)(ሐ)1 የተገለጸው የተሽከርካሪ እድሜ ከ15 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

B. **Competency requirement for Level 2 operator**

1/ The number of initial vehicles shall not be less than 30

2/ The vehicles age specified under sub-article (3) (1) (B) 1 of this Article shall not exceed 15 years.

3/ The loading capacity of the vehicle specified under sub-article (3) (1) (B) 2 of this Article shall not be less than 30 tons.

4/ The vehicles referred to under sub-article (3) (1) (B) 1, (3) (1) (B) 2 and (3) (1) (B) 3 of this Article shall be able to lift at least 900 tons at a time.

5/ If the requirements specified under sub-articles (3) (1) (B) 1, (3) (1) (B) 2 and (3) (1) (B) 3 of this Article are met, it may hold other vehicles not older than 30 years of age and other vehicles with a load capacity of not less than 20 tons

C. **Competency requirement for Level 3 operator**

1/ The number of initial vehicles shall not be less than 20.

2/ The vehicles age specified under sub-article (3) (1) (C) 1 of this Article shall not exceed 15 years.

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(1)(ሐ)2 የመጫን አቅም ከ 30 ቶን ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(1)(ሐ)1፣ (3)(1)(ሐ)2 እና (3)(1)(ሐ)3 የተገለጹትን ተሽከርካሪዎች በአንድ ጊዜ የማንሳት አቅማቸው ከ600 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፣
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(1)(ሐ)1፣ (3)(1)(ሐ)2 እና (3)(1)(ሐ)3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጠ ተሽከርካሪዎችን እና ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ ተሽከርካሪዎችን ሊይዝ ይችላል፡፡

መ. <u>ደረጃ4 የኦፐሬተር የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት</u>

1. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት ቢያንስ 10 መሆን አለበት፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(1)(መ)1 የተገለጸው የተሽከርካሪ እድሜ ከ10 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(1)(መ)2 የመጫን አቅም ከ3.5-20 ቶን ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(1)(መ)1፣ (3)(1)(መ)2 እና (3)(1)(መ)3 የተገለጹትን ተሽከርካሪዎች በአንድ ጊዜ ጭነት የማንሳት አቅማቸው ከ35 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፣

3/ The loading capacity of the vehicle specified under sub-article (3) (1) (C) 2 of this Article shall not be less than 30 tons.

4/ The vehicles referred to under sub-article (3) (1) (C) 1, (3) (1) (C) 2 and (3) (1) (C) 3 of this Article shall be able to lift at least 600 tons at a time.

5/ If the requirements specified under sub-articles (3) (1) (C) 1, (3) (1) (C) 2 and (3) (1) (C) 3 of this Article are met, it may hold other vehicles not older than 30 years of age and other vehicles with a load capacity of not less than 20 tons.

**D. <u>Competency requirement for Level 4 operator</u>**

1/ The number of initial vehicles shall not be less than 10.

2/ The vehicles age specified under sub-article (3) (1) (D) 1 of this Article shall not exceed 10 years.

3/ The loading capacity of the vehicle specified under sub-article (3) (1) (D) 2 of this Article shall be 3.5-20 tons.

4/ The vehicles referred to under sub-article (3) (1) (D) 1, (3) (1) (D) 2 and (3) (1) (D) 3 of this Article shall be able to lift at least 35 tons at a time.

**ሠ. ደረጃ 5 (የሀገር ውስጥ) የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት**

1. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት ቢያንስ 5 መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(1)(ሠ)1 የተገለጸው የተሽከርካሪ እድሜ ያልተገደበ ነው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(1)(ሠ)2 የመጫን አቅም ከ 7 ቶን ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(1)(ሠ)1፣ (3)(1)(ሠ)2 እና (3)(1)(ሠ)3 የተገለጹትን ተሽከርካሪዎች በአንድ ጊዜ ጭነት የማንሳት አቅማቸው ከ35 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፣

2. **ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር**

**ሀ. ደረጃ 1 የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት**

1. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት ቢያንስ 30 መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(2)(ሀ)1 የተገለጸው የተሽከርካሪ እድሜ ከ15 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(2)(ሀ)2 የመጫን አቅም ከ 30 ቶን ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(2)(ሀ)1፣ (3)(2)(ሀ)2 እና (3)(2)(ሀ)3 የተገለጹትን ተሽከርካሪዎች በአንድ ጊዜ የማንሳት አቅማቸው ከ900 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

**E. Competency requirement for Level 5/ Cross country road transport / operator**

1/ The number of initial vehicles shall not be less than 5.

2/ The vehicles age specified under sub-article (3) (1) (E) 1 of this Article is unlimited.

3/ The loading capacity of the vehicle specified under sub-article (3) (1) (E) 2 of this Article shall not be less than 7 tons.

4/ The vehicles referred to under sub-article (3) (1) (E) 1, (3) (1) (E) 2 and (3) (1) (E) 3 of this Article shall be able to lift at least 35 tons at a time.

2/ **For a Private limited company**

**A. competency requirement for Level 1 operator**

1/ The number of initial vehicles shall not be less than 30

2/ The vehicles age specified under sub-article (3) (2) (A) 1 of this Article shall not exceed 15 years.

3/ The loading capacity of the vehicle specified under sub-article (3) (2) (A) 2 of this Article shall not be less than 30 tons.

4/ The vehicles referred to under sub-article (3) (2) (A) 1, (3) (2) (A) 2 and (3) (2) (A) 3 of this Article shall be able to lift at least 900 tons at a time.

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(2)(ሀ)1፣ (3)(2)(ሀ)2 እና (3)(2)(ሀ)3 የተገለጹትን መስፈርተቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጡ ተሸከርካሪዎችን እና ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ ተሸከርካሪዎችን በባለቤትነት ሊይዝ ይችላል፡፡

**ለ. <u>ደረጃ 2 የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት</u>**

1. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት ቢያንስ 20 መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(2)(ለ)1 የተገለጸው የተሽከርካሪ እድሜ ከ15 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(2)(ለ)(2) የመጫን አቅም ከ 30 ቶን ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(2)(ለ)1፣ (3)(2)(ለ)2 እና (3)(2)(ለ)3 የተገለጹትን ተሸከርካሪዎች በአንድ ጊዜ ጭነት የማንሳት አቅማቸው ከ600 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፣
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(2)(ለ)1፣ (3)(2)(ለ)2 እና (3)(2)(ለ)3 የተገለጹትን መስፈርተቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጡ ተሸከርካሪዎችን እና ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ ተሸከርካሪዎችን ሊይዝ ይችላል፡፡

**5/** If the requirements specified under sub-articles (3) (2) (A) 1, (3) (2) (A) 2 and (3) (2) (A) 3 of this Article are met, it may hold other vehicles not older than 30 years of age and other vehicles with a load capacity of not less than 20 tons.

**B. <u>Competency requirement for Level 2 operator</u>**

**1/** The number of initial vehicles shall not be less than 20

**2/** The vehicles age specified under sub-article (3) (2) (B) 1 of this Article shall not exceed 15 years.

**3/** The loading capacity of the vehicle specified under sub-article (3) (2) (B) 2 of this Article shall not be less than 30 tons.

**4/** The vehicles referred to under sub-article (3) (2) (B) 1, (3) (2) (B) 2 and (3) (2) (A) 3 of this Article shall be able to lift at least 600 tons at a time.

**5/** If the requirements specified under sub-articles (3) (2) (B) 1, (3) (2) (B) 2 and (3) (2) (B) 3 of this Article are met, it may hold other vehicles not older than 30 years of age and other vehicles with a load capacity of not less than 20 tons.

**ሐ. <u>ደረጃ3 የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት</u>**

1. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት ቢያንስ 10 መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(2)(ሐ)1 የተገለጸው የተሽከርካሪ እድሜ ከ15 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(2)(ሐ)2 የመጫን አቅም ከ 30 ቶን ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(2)(ሐ)1፣ (3)(2)(ሐ)2 እና (3)(2)(ሐ)3 የተገለጹትን ተሽከርካሪዎች በአንድ ጊዜ የማንሳት አቅማቸው ከ300 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፣
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3)(2)(ሐ)1፣ (3)(2)(ሐ)2 እና (3)(2)(ሐ)3 የተገለጹትን መስፈርተቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጡ ተሽከርካሪዎችን እና ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ ተሽከርካሪዎችን ሊይዝ ይችላል፡፡

**መ. <u>ደረጃ4 የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት</u>**

1. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት ቢያንስ 10 መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(2)(መ)1 የተገለጸው የተሽከርካሪ እድሜ ከ10 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

**C. <u>Competency requirement for Level 3 operator</u>**

**1/** The number of initial vehicles shall not be less than 10

**2/** The vehicles age specified under sub-article (3) (2) (C) 1 of this Article shall not exceed 15 years.

**3/** The loading capacity of the vehicle specified under sub-article (3) (2) (C) 2 of this Article shall not be less than 30 tons.

**4/** The vehicles referred to under sub-article (3) (2) (C) 1, (3) (2) (C) 2 and (3) (2) (C) 3 of this Article shall be able to lift at least 300 tons at a time.

**5/** If the requirements specified under sub-articles (3) (2) (C) 1, (3) (2) (C) 2 and (3) (2) (C) 3 of this Article are met, it may hold other vehicles not older than 30 years of age and other vehicles with a load capacity of not less than 20 tons.

**D. <u>Competency requirement for Level 4 operator</u>**

**1/** The number of initial vehicles shall not be less than 10.

**2/** The vehicles age specified under sub-article (3) (2) (D) 1 of this Article shall not exceed 10 years.

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(2)(መ)2 የመጫን አቅም ከ 3.5-20 ቶን ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(2)(መ)1፣ (3)(2)(መ)2 እና (3)(2)(መ)3 የተገለጹትን ተሽከርካሪዎች በአንድ ጊዜ ጭነት የማንሳት አቅማቸው ከ35 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፣

**ሠ. <u>ደረጃ 5 (የሀገር ውስጥ) የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት</u>**

1. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት ቢያንስ 5 መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(2)(ሠ)1 የተገለጸው የተሽከርካሪ እድሜ ከ20 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(2)(ሠ)2 የመጫን አቅም ከ 7 ቶን ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(2)(ሠ)1፣ (3)(2)(ሠ)2 እና (3)(2)(ሠ)3 የተገለጹትን ተሽከርካሪዎች በአንድ ጊዜ ጭነት የማንሳት አቅማቸው ከ35 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት።

**3/** The loading capacity of the vehicle specified under sub-article (3) (2) (D) 2 of this Article shall be 3.5-20 tons.

**4/** The vehicles referred to under sub-article (3) (2) (D) 1, (3) (2) (D) 2 and (3) (2) (D) 3 of this Article shall be able to lift at least 35 tons at a time.

**E. <u>Competency requirement for Level 5/ Cross country road transport / operator</u>**

**1/** The number of initial vehicles shall not be less than 5

**2/** The vehicles age specified under sub-article (3) (2) (E)1 of this Article is unlimited.

**3/** The loading capacity of the vehicle specified under sub-article (3) (2) (E) 2 of this Article shall not be less than 7 tons.

**4/** The vehicles referred to under sub-article (3) (2) (E) 1, (3) (2) (E) 2 and (3) (2) (E) 3 of this Article shall be able to lift at least 35 tons at a time.

3. **ለግል ትራንስፖርት ኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት፣**

**ሀ. ደረጃ1 የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት**

1. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት ቢያንስ 25 መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(3)(ሀ)1 የተገለጸው የተሽከርካሪ እድሜ ከ15 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(3)(ሀ)2 የመጫን አቅም ከ 30 ቶን ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(3)(ሀ)1፣ (3)(3)(ሀ)2 እና (3)(3)(ሀ)3 የተገለጹትን ተሽከርካሪዎች በአንድ ጊዜ የማንሳት አቅማቸው ከ750 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፣
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(3)(ሀ)1፣ (3)(3)(ሀ)2 እና (3)(3)(ሀ)3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጡ ተሽከርካሪዎችን እና ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት ሊይዝ ይችላል፡፡

**ለ. ደረጃ 2 የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት**

1. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት ቢያንስ 15 መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(3)(ለ)1 የተገለጸው የተሽከርካሪ እድሜ ከ15 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

3/ **For a Sole proprietorship**

**A. Competency requirement for Level 1 operator**

1/ The number of initial vehicles shall not be less than 25

2/ The vehicles age specified under sub-article (3) (3) (A) 1 of this Article shall not exceed 15 years.

3/ The loading capacity of the vehicle specified under sub-article (3) (3) (A) 2 of this Article shall not be less than 30 tons.

4/ The vehicles referred to under sub-article (3) (3) (A) 1, (3) (3) (A) 2 and (3) (3) (A) 3 of this Article shall be able to lift at least 750 tons at a time.

5/ If the requirements specified under sub-articles (3) (3) (A) 1, (3) (3) (A) 2 and (3) (3) (A) 3 of this Article are met, it may hold other vehicles not older than 30 years of age and other vehicles with a load capacity of not less than 20 tons.

**B. Competency requirement for Level 2 operator**

1/ The number of initial vehicles shall not be less than 15

2/ The vehicles age specified under sub-article (3) (3) (B) 1 of this Article shall not exceed 15 years

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(3)(ለ)2 የመጫን አቅም ከ 30 ቶን ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(3)(ለ)1፣ (3)(3)(ለ)2 እና (3)(3)(ለ)3 የተገለጹትን ተሽከርካሪዎች በአንድ ጊዜ ጭነት የማንሳት አቅማቸው ከ450 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፣
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(3)(ለ)1፣ (3)(3)(ለ)2 እና (3)(3)(ለ)3 የተገለጹትን መስፈርተቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ያልበለጡ ተሽከርካሪዎችን እና ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ ተሽከርካሪዎችን ሊይዝ ይችላል፡፡

### ሐ. <u>ደረጃ3 የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት</u>

1. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት ቢያንስ 5 መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(3)(ሐ)1 የተገለጸው የተሽከርካሪ እድሜ ከ15 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(3)(ሐ)2 የመጫን አቅም ከ 30 ቶን ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(3)(ሐ)1፣ (3)(3)(ሐ)2 እና (3)(3)(ሐ)3 የተገለጹትን ተሽከርካሪዎች በአንድ ጊዜ ጭነት የማንሳት አቅማቸው ከ150 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፣
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(3)(ሐ)1፣ (3)(3)(ሐ)2 እና (3)(3)(ሐ)3 የተገለጹትን መስፈርቶች ካሟላ ሌሎች እድሜያቸው ከ30 ዓመት ያልበለጡ ተሽከርካሪዎችን እና ሌሎች የመጫን አቅማቸው ከ20 ቶን ያላነሰ ተሽከርካሪዎችን በባለቤትነት ሊይዝ ይችላል፡፡

**3/** The loading capacity of the vehicle specified under sub-article (3) (3) (B) 2 of this Article shall not be less than 30 tons.

**4/** The vehicles referred to under sub-article (3) (3) (B) 1, (3) (3) (B) 2 and (3) (3) (A) 3 of this Article shall be able to lift at least 450 tons at a time.

**5/** If the requirements specified under sub-articles (3) (3) (B) 1, (3) (3) (B) 2 and (3) (3) (B) 3 of this Article are met, it may hold other vehicles not older than 30 years of age and other vehicles with a load capacity of not less than 20 tons.

### C. <u>Competency requirement for Level 3 operator</u>

**1/** The number of initial vehicles shall not be less than 5.

**2/** The vehicles age specified under sub-article (3) (3) (C) 1 of this Article shall not exceed 15 years.

**3/** The loading capacity of the vehicle specified under sub-article (3) (3) (C) 2 of this Article shall not be less than 30 tons.

**4/** The vehicles referred to under sub-article (3) (3) (C) 1, (3) (3) (C) 2 and (3) (3) (C) 3 of this Article shall be able to lift at least 150 tons at a time.

**5/** If the requirements specified under sub-articles (3) (3) (C) 1, (3) (3) (C) 2 and (3) (3) (C) 3 of this Article are met, it may hold other vehicles not older than 30 years of age and other vehicles with a load capacity of not less than 20 tons

**መ. <u>ደረጃ4 የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት</u>**

1. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት ቢያንስ 5 መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(3)(መ)1 የተገለጸው የተሽከርካሪ እድሜ ከ10 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(3)(መ)2 የመጫን አቅም ከ 3.5-20 ቶን ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(3)(መ)1፣ (3)(3)(መ)2 እና (3)(3)(መ)3 የተገለጹት ተሽከርካሪዎች በአንድ ጊዜ ጭነት የማንሳት አቅማቸው ከ21 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፣

**ሠ. <u>ደረጃ 5 (የሀገር ውስጥ) የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ መስፈርት</u>**

1. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት ቢያንስ 5 መሆን አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(3)(ሠ)1 የተገለጸው የተሽከርካሪ እድሜ ያልተገደበ ነው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(3)(ሠ)2 የመጫን አቅም ከ 7 ቶን ያላነሰ መሆን ይኖርበታል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(3)(ሠ)1፣ (3)(3)(ሠ)2 እና (3)(3)(ሠ)3 የተገለጹትን ተሽከርካሪዎች በአንድ ጊዜ ጭነት የማንሳት አቅማቸው ከ35 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፣

**D. <u>Competency requirement for Level 4 operator</u>**

1/ The number of initial vehicles shall not be less than 5.

2/ The vehicles age specified under sub-article (3) (3) (D) 1 of this Article shall not exceed 10 years.

3/ The loading capacity of the vehicle specified under sub-article (3) (3) (D) 2 of this Article shall be 3.5-20 tons.

4/ The vehicles referred to under sub-article (3) (3) (D) 1, (3) (3) (D) 2 and (3) (3) (D) 3 of this Article shall be able to lift at least 21 tons at a time.

**E. <u>Competency requirement for Level 5/Cross country road transport/ operator</u>**

1/ The number of initial vehicles shall not be less than 5.

2/ The vehicles age specified under sub-article (3) (3) (E) 1 of this Article is unlimited.

3/ The loading capacity of the vehicle specified under sub-article (3) (3) (E) 2 of this Article shall not be less than 7 tons.

4/ The vehicles referred to under sub-article (3) (3) (E) 1, (3) (3) (E) 2 and (3) (3) (E) 3 of this Article shall be able to lift at least 35 tons at a time.

4. **ለግል ንግድ (የምዝገባ ፈቃድ)**

ሀ. የመነሻ የተሽከርካሪ ብዛት 1 ነው፡፡

ለ.የተሽከርካሪው የአገልግሎት ዘመን ከ30 ዓመት ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

ሐ.በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ (3)(4)1 እና (3)(4)2 የተሽከርካሪዎች የመጫን አቅም ከ 20 ቶን ያላነሰ መሆን አለበት፡፡

9. **የጭነት ትራንስፖርት ኦፕሬተሮች የአገልግሎት ወሰን**

1. **የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ ማህበራት**

ሀ. በደረጃ 1 ወይም በደረጃ 2 ወይም በደረጃ 3 የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ ማህበራት በሀገር አቋራጭ እና በአለም-ዓቀፍ የመንገድ ጭነት ማመላለሻ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት ይችላሉ፡

ለ. በደረጃ 4 የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ ማህበራት በሀገር አቋራጭ የመንገድ ጭነት ማመላለሻ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቻ የሚሰጡ ይሆናል፡፡

2. **የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ ድርጅቶች**

ሀ. በደረጃ 1 ወይም በደረጃ 2 ወይም በደረጃ 3 የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ ድርጅቶች በሀገር አቋራጭ እና በአለም-ዓቀፍ የመንገድ ጭነት ማመላለሻ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት ይችላሉ፣

4/ **Private Commercial /Registration Licence/**

a) The number of initial vehicle is 1

b) Vehicle age shall not exceed 30 years

c) The loading capacity of the vehicle specified under sub-article (3) (4) 1 and (3) (4) 2 of this Article shall not be less than 20 tons.

9. **Service Scope of Freight Transport Operators**

1. **Associations that have received operator competency Licence**

a. Associations with Level One operator competency Licence or Level Two operator competency Licence or Level Three operator competency Licence Operating Qualifications may be able to provide cross-country and international road freight transport services.

b. Associations with Level four operator competency Licence shall only provide cross-country road freight transport services.

2. **Companies that have received operator competency Licence**

a. Companies with Level one operator competency Licence or Level two operator competency Licence or Level three operator competency Licence Operating Qualifications may be able to provide cross-country and international road freight transport services.

ለ. በደረጃ 4 የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ ድርጅቶች በአለም-ዓቀፍ የመንገድ ጭነት ማመላለሻ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቻ የሚሰጡ ሲሆን ተሽከርካሪዎቹ ኢ.ት ሰሌዳ መለጠፍ አለባቸው፣

ሐ. በደረጃ 5 የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ ድርጅቶች አገልግሎት መስጠት የሚችሉት የሀገር አቋራጭ የመንገድ ጭነት ማመላለሻ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቻ ነው፣

3. <u>**የኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ የግል ትራንስፖርተሮች**</u>

ሀ. በደረጃ 1፣ በደረጃ 2፣ ወይም በደረጃ 3 የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ ድርጅቶች በሀገር አቋራጭ እና በአለም-ዓቀፍ የመንገድ ጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት ይችላሉ፣

ለ. በደረጃ 4 የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ ድርጅቶች በአለም-ዓቀፍ የመንገድ ጭነት ማመላለሻ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቻ የሚሰጡ ሲሆን ተሽከርካሪዎቹ ኢ.ት ሰሌዳ መለጠፍ አለባቸው፣

ሐ. በደረጃ 5 የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ የወሰዱ ድርጅቶች አገልግሎት መስጠት የሚችሉት የሀገር አቋራጭ የመንገድ ጭነት ማመላለሻ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቻ ነው፣

**b.** Companies with Level four operator competency Licence shall only provide international road freight transport services and the vehicles shall have ET number plate.

**c.** Companies with Level five operator competency Licence shall only provide cross-country road freight transport services.

3. <u>**Sole proprietor that have received operator competency Licence**</u>

**a.** Sole proprietor with Level one operator competency Licence or Level two operator competency Licence or Level three operator competency Licence Operating Qualifications may be able to provide cross-country and international road freight transport services.

**b.** Sole proprietor with Level four operator competency Licence shall only provide international road freight transport services and the vehicles shall have ET number plate.

**c.** Sole proprietor with Level five operator competency Licence shall only provide cross-country road freight transport services.

4. ግል ንግድ

ሀ. በግል ንግድ ትራንስፖርት አገልግሎት ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የራሳቸውን ምርት ወይም ግብዓት በራሳቸው ተሽከርካሪ ብቻ የሚያጓጉዙ ሲሆን የሀገር አቋራጭ እና የአለም-ዓቀፍ የመንገድ ጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት ላይ ሊሰማሩ ይችላሉ፡፡

ለ. የግል ንግድ የጭነት ትራንስፖርት ተሽከርካሪዎች የንግድ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት አይችሉም፡፡

10. የሰው ኃይል አደረጃጀት፡-

1. ለማህበር (ከደረጃ 1 እስከ 4)

ሀ. ዋና ሥራ አስኪያጅ፡ የመጀመሪያ ድግሪና ከዚያ በላይ በትራንስፖርት ማኔጅመንት፣ በትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ፣ በኢኮኖሚክስ፣ ሊደርሺፕ፣ በሎጂስቲክስ፣ በቢዝነስ አስተዳደር፣ በማኔጅመንት እና በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ እና በትራንስፖርት ዘርፍ በመጀመሪያ ዲግሪ 6 ዓመት፣ በሁለተኛ ዲግሪ /ማስተርስ/ 4 ዓመት እና ከዚያ በላይ የስራ ልምድ ያለው፣

ለ. የኦፕሬሽንና ገበያ ጥናት ሥራ አስኪያጅ፡ የመጀመሪያ ድግሪና ከዚያ በላይ በትራንስፖርት ማኔጅመንት፣ በትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ፣ በኢኮኖሚክስ፣ ሊደርሺፕ፣ በሎጂስቲክስ፣ በቢዝነስ አስተዳደር፣ በማኔጅመንት እና በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ እና በትራንስፖርት ዘርፍ በመጀመሪያ ዲግሪ 4 ዓመት፣ በሁለተኛ ዲግሪ /ማስተርስ/ 2 ዓመት እና ከዚያ በላይ ልምድ ያለው፣

4. **Private commercial**

a. Private commercial transport services persons or Companies transport their products only in their own vehicles and may operate cross-country and international road freight transport.

b. Private commercial freight vehicles shall not provide commercial road freight transport services.

10. **Personnel Organization:**

1. **For Association (Levels 1 to Level 4)**

a. **General Manager:** First Degree and above in Transport Management, Transport Economics, Economics, Leadership, logistics, Business management, management and related fields; work experience 6 years in Degree and 4 years in Master's;

b. **Operation and Market Research Manager:** First Degree and above in Transport Management, Transport Economics, Economics, Leadership, logistics, Business management, management and related fields; work experience 4 years in Degree and 2 years in Master's;

ሐ. **<u>የአስተዳደርና ፋይናንስ ኃላፊ፡</u>** የመጀመሪያ ድግሪ/ዲፕሎማ በማኔጅመንት፣ በኢኮኖሚክስ፣ በአካውንቲንግ፣ በቢዝነስ አስተዳደር ወይም ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ እና በቂ የስራ ልምድ ያለው፣

መ. **<u>የኦፕሬሽን ስምሪት ክትትልና ዕቅድ ባለሙያ፡</u>** የመጀመሪያ ድግሪ/ዲፕሎማ በትራንስፖርት ማኔጅመንት፣ በትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ፣ በኢኮኖሚክስ፣ ሊደርሺፕ፣ በሎጂስቲክስ፣ በቢዝነስ አስተዳደር፣ አይቲ፣ በማኔጅመንት እና በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ እና በትራንስፖርት ዘርፍ 1 ዓመትና ከዚያ በላይ የስራ ልምድ ያለው፣

ሠ. **<u>የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ግንዛቤ ባለሙያ፡</u>** የመጀመሪያ ድግሪ/ዲፕሎማ በትራንስፖርት ማኔጅመንት፣ በትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ፣ በሳይኮሎጂ፣ በኢኮኖሚክስ፣ በሎጂስቲክስ፣ በቢዝነስ አስተዳደር፣ በማኔጅመንት ወይም በተመሳሳይ የትምህርት አይነት 2 ዓመት የስራ ልምድ ያለው፣

ረ. **<u>አስፈላጊ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሠራተኞች፡</u>** የመጀመሪያ ድግሪ/ዲፕሎማ በትራንስፖርት ማኔጅመንት፣ በትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ፣ በኢኮኖሚክስ፣ በሎጂስቲክስ፣ በቢዝነስ አስተዳደር፣ በማኔጅመንት ወይም በተመሳሳይ የትምህርት አይነት እና 2 ዓመት የስራ ልምድ ያለው፣

c. **<u>Head of Administration and Finance</u>** First Degree/Diploma in Management, Economics, Accounting, Business Administration and related fields work experience 4 years in Degree and 2 years in Diploma;

d. **<u>Trip operation, Follow-up and planning expert</u>** First Degree/Diploma in Transport Management, Transport Economics, Economics, Leadership, logistics, Business management, IT, management and related fields; work experience 1 years and above;

e. **<u>Road Traffic safety awareness expert</u>**: First Degree/Diploma in Transport Management, Transport Economics, psychology, Economics, logistics, Business management, management and related fields; work experience 2 years and above;

f. **<u>Necessary branch offices staff:</u>** First Degree/Diploma in Transport Management, Transport Economics, Economics, logistics, Business management, management and related fields; work experience 2 years and above;

2. **ለድርጅት (ከደረጃ1-5)**

ሀ. ለዚህ አንቀጽ አተገባበር ድርጅት ማለት አክሲዮን ማህበር እና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ነው።

ለ. ድርጅቶች ከስራ አስኪያጅ ጀምሮ የየራሳቸውን የሰው ኃይል አደረጃጀት የመወሰንና የማዋቀር ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን ቢያንስ ስራ አስኪያጅ፣ የኦፕሬሽንና ስምሪት ባለሙያ እና የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ግንዛቤ ባለሙያ ማካተት አለበት፡፡

ሐ. አደራጅ አካሉ በየጊዜው ወይም በማንኛውም ጊዜ በሚያደርገው ክትትልና ቁጥጥር የአንድ ድርጅቶት የሰው ኃይል አደረጃጀት የኦፐሬተርነት ፈቃድ የተሰጠበትን አገልግሎት ለመስጠት በማያስችለው ደረጃ ላይ መሆኑን ካረጋገጠ ለድርጅቱ የተሰጠውን ደረጃ ሊቀንስ፣ ሊያሻሽል ወይም ለድርጅቱ የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ ሊሰርዘው ይችላል።

መ. አደራጁ አካል በዚህ አንቀጽ ፊደል (ሐ) የተመለከተውን እርምጃ ከመውሰዱ በፊት ለድርጅቱ የሰው ኃይል አደረጃጀቱን እንዲያስተካክል ከ1 ወር ያልበለጠ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይችላል።

2. **For Companies (Levels 1 to 5)**

a. For the purpose of this Article Company means Share Companies and Private Limited Companies,

b. Companies have the responsibility to organizing their personnel and shall at least including the General Manager, Trip operation expert and Road Traffic safety awareness expert.

c. Where, upon its regular or random inspection, the Establishing Organ finds the personnel organizational structure of a Company to be unfit to operate the business it is licensed for the Establishing Organ may demote, revise or cancel the registration of the Operator.

d. In exercising its authority as stipulated under (c) above, the Establishing Organ may give a prior notice of not more than 1 month to the Company to rectify the findings.

3. **ለግል ትራንስፖርት (ከደረጃ 1-2)**

ሀ. **ዋና ሥራ አስኪያጅ፡** የመጀመሪያ ድግሪና ከዚያ በላይ በትራንስፖርት ማኔጅመንት፣ በትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ፣ በኢኮኖሚክስ፣ ሊደርሺፕ፣ በሎጂስቲክስ፣ በቢዝነስ አስተዳደር፣ በማኔጅመንት እና በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ እና በትራንስፖርት ዘርፍ በመጀመሪያ ዲግሪ 6 ዓመት፣ በሁለተኛ ዲግሪ /ማስተርስ/ 4 ዓመት እና ከዚያ በላይ የስራ ልምድ ያለው፣

ለ. **የኦፕሬሽንና ገበያ ጥናት ሥራ አስኪያጅ፡** የመጀመሪያ ድግሪና ከዚያ በላይ በትራንስፖርት ማኔጅመንት፣ በትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ፣ በኢኮኖሚክስ፣ ሊደርሺፕ፣ በሎጂስቲክስ፣ በቢዝነስ አስተዳደር፣ በማኔጅመንት እና በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ እና በትራንስፖርት ዘርፍ በመጀመሪያ ዲግሪ 4 ዓመት፣ በሁለተኛ ዲግሪ /ማስተርስ/ 2 ዓመት እና ከዚያ በላይ በቂ ልምድ ያለው፣

ሐ. **የአስተዳደርና ፋይናንስ ኃላፊ፡** የመጀመሪያ ድግሪ/ዲፕሎማ በማኔጅመንት፣ በኢኮኖሚክስ፣ በአካውንቲንግ፣ በቢዝነስ አስተዳደር/ተመሳሳይ በቂ ልምድ ያለው፣

መ. **የኦፕሬሽንና ስምሪት ክትትልና ዕቅድ ባለሙያ፡** የመጀመሪያ ድግሪ/ዲፕሎማ በትራንስፖርት ማኔጅመንት፣ በትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ፣ በኢኮኖሚክስ፣ ሊደርሺፕ፣ በሎጂስቲክስ፣ በቢዝነስ አስተዳደር፣ አይቲ፣ በማኔጅመንት እና በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ እና በትራንስፖርት ዘርፍ 1 ዓመትና ከዚያ በላይ ልምድ ያለው፣

3. **For Sole proprietorship (Level 1 to Level 2)**

a. **General Manager:** First Degree and above in Transport Management, Transport Economics, Economics, Leadership, logistics, Business management, management and related fields; work experience 6 years in Degree and 4 years in Master's;

b. **Operation and Market Research Manager**: First Degree and above in Transport Management, Transport Economics, Economics, Leadership, logistics, Business management, management and related fields; work experience 4 years in Degree and 2 years in Master's;

c. **Head of Administration and Finance**: First Degree/Diploma in Management, Economics, Accounting, Business Administration and related fields relevant work experience;

d. **Trip operation, Follow-up and planning expert** First Degree/Diploma in Transport Management, Transport Economics, Economics, Leadership, logistics, Business management, IT, management and related fields; work experience 1 years and above;

**ሠ. የመንገድ ደህንነት ግንዛቤ ባለሙያ፡** የመጀመሪያ ድግሪ/ዲፕሎማ በትራንስፖርት ማኔጅመንት፣ በትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ፣ በሳይኮሎጂ፣ በኢኮኖሚክስ፣ በሎጂስቲክስ፣ በቢዝነስ አስተዳደር፣ በማኔጅመንት እና በተመሳሳይ የትምህርት አይነት 2 ዓመት የስራ ልምድ ያለው፣

**ረ. አስፈላጊ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሠራተኞች፡** የመጀመሪያ ድግሪ/ዲፕሎማ በትራንስፖርት ማኔጅመንት፣ በትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ፣ በኢኮኖሚክስ፣ በሎጂስቲክስ፣ በቢዝነስ አስተዳደር፣ በማኔጅመንት እና በተመሳሳይ የትምህርት አይነትና 2 ዓመት የስራ ልምድ ያለው፣

4. **ለግል ትራንስፖርት (ከደረጃ 3 - 5)**

**ሀ. የኦፕሬሽን ባለሙያ**፡ የመጀመሪያ ድግሪና ከዚያ በላይ በትራንስፖርት ማኔጅመንት፣ በትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ፣ በኢኮኖሚክስ፣ ማርኬቲነግ፣ ሊደርሺፕ፣ በሎጂስቲክስ፣ በቢዝነስ አስተዳደር፣ በማኔጅመንት እና በተመሳሳይ የትምህርት ዘርፍ እና በትራንስፖርት ዘርፍ 4 ዓመትና ከዚያ በላይ የስራ ልምድ ያለው፣

**ለ. የአስተዳደርና ፋይናንስ ባለሙያ፡** የመጀመሪያ ድግሪ/ዲፕሎማ በማኔጅመንት፣ በኢኮኖሚክስ፣ በአካውንቲንግ፣ በቢዝነስ አስተዳደር/ተመሳሳይ የስራ ልምድ ያለው፣

e. **Road Traffic safety awareness expert**: First Degree/Diploma in Transport Management, Transport Economics, psychology, Economics, logistics, Business management, management and related fields; work experience 2 years and above;

f. **Necessary branch offices staff:** First Degree/Diploma in Transport Management, Transport Economics, Economics, logistics, Business management, management and related fields; work experience 2 years and above;

4. **For Sole proprietorship (Level 3 to Level 5)**

a. **Operation expert:** First Degree and above in Transport Management, Transport Economics, Economics, Marketing, Leadership, logistics, Business management, management and related fields; work experience 4 years and above;

b. **Administration and Finance expert:** First Degree/Diploma in Management, Economics, Accounting, Business Administration and related fields relevant work experience;

**ሐ. የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ግንዛቤ ባለሙያ፡** የመጀመሪያ ድግሪ/ዲፕሎማ በትራንስፖርት ማኔጅመንት፣ በትራንስፖርት ኢኮኖሚክስ፣ በሳይኮሎጂ፣ በኢኮኖሚክስ፣ በሎጂስቲክስ፣ በቢዝነስ አስተዳደር፣ በማኔጅመንት እና በተመሳሳይ የትምህርት አይነት፣

## 11. ቢሮና የቢሮ መገልገያ መሳሪያዎችና ሕትመቶችን በተመለከተ፣

1. አድራሻው በግልጽ የሚታወቅ ቢሮ
2. የኢንተርኔት አገልግሎት
3. ቀጥታ የስልክ መስመር ወይም ሞባይል
4. ቲተርና ክብ ማህተም፣
5. የተሽከርካሪ የጭነት ማዘዣ ሠነድ (FO)
6. የተሽከርካሪ እንቅስቃሴ መከታተያና መቆጣጠሪያ /Log Book/
7. የገንዘብ መቀበያና የወጪ ማዘዣ ሠነዶች
8. ባለስልጣኑ መ/ቤት በሚያወጣው ስታንዳርድ መሰረት የማህበሩን/ድርጅቱን ስምና አርማ የያዘ ስቲከር
9. ሌሎች ለሥራ የሚያስፈልጉ ተጨማሪ ሠነዶች ካሉ ኮፒውን ይያዛል፡፡

c. **Road Traffic safety awareness expert:** First Degree/Diploma in Transport Management, Transport Economics, psychology, Economics, logistics, Business management, management and related fields;

## 11. Office Facility and Equipment;

1. well known Office address
2. Internet service
3. Direct telephone or mobile
4. Signature stamp and seal,
5. Vehicle Freight Order Document (FO)
6. Vehicle follow-up and control/Log Book/
7. Receipt and expense order documents
8. Sticker bearing the name and logo of the Association or the Enterprise in accordance with the standard issued by the Authority
9. If there are other additional documents required for the work, a copy shall be attached.

## 12.የደረጃ ማሻሻያ እና ክለሳ

በመስፈርቱ መሠረት ደረጃ የተሰጠው ኦፕሬተር በአደራጅ አካሉ ፈቃዱ ሲታደስ እየተገመገመ እንዲሁም በማንኛውም ጊዜ በክትትል ሲገኝና ሲረጋገጥ በዚህ መመሪያ የተቀመጡትን ነጥቦች አሻሽሎ ወይም አጓድሎ ከተገኘ በአደራጅ አካሉ ደረጃው ሊሻሻል ወይም ሊከለስ ይችላል፡፡

## ክፍል አራት

## ለኦፕሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ስለሚቀርብ ማመልከቻ፣ የምዝገባ እድሳት እና የአገልግሎት ክፍያ

## 13.የብቃት ማረጋገጫ ማመልከቻ

1. በዚህ መመሪያ መሠረት ኦፕሬተር ሆኖ የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት የሚፈልግ ሰው በአደራጁ አካል የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ ሞልቶ ማቅረብ አለበት፣
2. የማመልከቻ ፎርሙ በትክክል መሞላትና በቅጹ ውስጥ ከሚያስፈልጉት መረጃዎች እና ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ ያለበት ሆኖ፡

ሀ. የትራንስፖርት ኦፕሬተር በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 ከንዑስ-አንቀጽ (1) እስከ (4) መሰረት ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 5 የተቀመጠዉን መነሻ የተሽከርካሪ ቁጥር እና ዝርዝር መስፈርት ሙሉ በሙሉ ተሟልቶ መገኘት አለበት፡፡

## 12. Improvement and Review of Level

Operator graded according to the requirement evaluating when the licence is renewed and monitored at any time, it may change the level if it finds any amendments or omission in this directive.

## Part Four

## Application for Certificate of Competence to be an Operator, Renewal and Service Fee

## 13. Application

1/ Any person intending to secure an Operator's Certificate of Competence in accordance with this Directive shall submit a completed application form as prepared by the Establishing Organ.

2/ the Application form shall be filled correctly and be submitted together with supporting documents as required by the form; and:

a. Shall meet the minimum number of vehicles and other details set for the Grades one to four as indicated under sub-articles (1) to (4) Article 11 of this Directive;

ለ. የኦፐሬተሩ ቋሚ ቢሮ ስለመዘጋጀቱና ቢሮው የግል ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ /ኮፒ/ የኪራይ ከሆነ ቢያንስ የአንድ ዓመት በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የተረጋገጠ ሕጋዊ የኪራይ ውል ከኮፒው ጋር ማቅረብ አለበት፤

ሐ. በመመሪያው መሰረት የተቀጠረ በቂ የሰው ኃይል ዝርዝርና የሕትመት ናሙና ሰነድ ኦሪጅናሉን ከኮፒ ጋር ማቅረብ አለበት፤

መ. የሰው ሀይል፣ የተሽከርካሪ ዝርዝር፣ የመገልገያ መሣሪያዎችና ሌሎችንም መረጃዎች አደራጁ አካል በሚሰጠው ፎርማት መሠረት ሞልቶና አረጋግጦ ያቀርባል፣

ሠ. በመሥፈርቱ የተዘረዘሩት ግዴታዎች፣ የቢሮ አደረጃጀትና የመገልገያ መሳሪያዎች በሡነድ መሟላታቸውን የሚያረጋግጥ በፊቃድ ጠያቂዉ ፊርማና ማህተም የተረጋገጠ ሰነድ ሲቀርብ ለአገልግሎት ጠያቂው ተቋም ወቅታዊ የደረጃ ምደባ ማስረጃ ይሰጣል፡፡

ረ. ማንኛውም ደረጃ የተሰጠው የጭነት ትራንስፖርት ኦፕሬተር የሙያ ሥነ-ምግባርን አክብሮ ለማገልገል ከዚህ መመሪያ ጋር አባሪ የተደረገውን ቅጽ አንብቦና ፈርሞ ማቅረብ አለበት።

b. Shall produce a copy of a title deed for the office in case the office is own property or a registered lease agreement envisaging at least a one year lease agreement for the office;

c. Shall produce details of personnel and sample publications as required by the Directive; and a copy thereof to be certified with the original;

d. Shall fill-in and attest on the format availed to it details of human resources, details of vehicles, utility equipment and other details;

e. Shall be issued with a Grade equivalent to the applicant's condition upon completion and submission of a signed and stamped application of the applicant;

f. Shall submit a completed and signed form as annexed to this Directive as to the observance of professional ethics by any Graded freight transport operator;

3. **<u>የአፈፃፀም ሁኔታ</u>**

1. አደራጅ አካሉ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 13 መሠረት የቀረበለትን ማመልከቻ ትክክለኛነት በመመዘን እና ሌሎች ቴክኒካል ነገሮችን ካረጋገጠ በኃላ አስፈላጊውን ያገልግሎት ክፍያ በማስከፈል አመልካቹ የሚያሟላውን የኦፕሬተርነት ብቃት ማጋገጫ ይሰጣል፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ-አንቀፅ (1) መሰረት የኦፕሬተርነት ብቃት ማጋገጫ መስጠት ካልተቻለ ያልተቻለበትን ምክንያት ከመጥቀስ ጋር ለአመልካቹ በፅሁፍ ይገለጽለታል።

**14.<u>የኦፕሬተር ምዝገባ ፈቃድ ዕድሳት</u>**

1. የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የወሰደ ማንኛውም ማኀበር በየዓመቱ ከመስከረም 1 ቀን እስከ የካቲት 30 ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን ክፍያ በመፈፀም ምዝገባውን ማሳደስ አለበት፣
2. የኦፕሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ የወሰደ ማንኛውም ድርጅት በየዓመቱ ከሐምሌ 1 ቀን እስከ ታሕሳስ 30 ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ አስፈላጊውን ክፍያ በመፈፀም ምዝገባውን ማሳደስ አለበት፣
3. መስፈርቱን አሟልተው ደረጃ የወሰዱ ኦፕሬተሮች በእድሳት ወቅት በመመሪያው የተቀመጠውን መነሻ የተሽከርካሪ ቁጥር ሙሉ ለሙሉ ወይም 100% አሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡

3/ **<u>Issuance</u>**

a. The Establishing Organ, upon evaluating the appropriateness of the application submitted to it and other technical requirements in accordance with Article 13 of this Directive, and by charging the applicable service fee shall issue the Operator’s Certificate of Competence;

b. Where the requested certificate can’t be issued, the Establishing Organ shall notify same to the applicant with justifications thereof.

**14<u>. Renewal of Operators Registration License</u>**

1/ Any Association issued with operator’s certificate of competence shall have it renewed every year within the periods from September 11 up to March 7 upon payment of the prescribed service fee;

2/ Any Company issued with operator’s certificate of competence shall have it renewed every year within the periods from July 8 up to January 7 upon payment of the prescribed service fee;

3/ Operators assigned with a specific level shall, during renewal of their license, meet fully or 100% the initial vehicle requirements set for that level in the Directive;

4. የተጠናቀቀው በጀት ዓመት የማህበር ሂሳብ በውጪ ኦዲተር ተመርምሮ በጠ/ጉባዔ ጸድቆ ከአመታዊ የማህበሩ ዝርዝር የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት በዕድሳት ወቅት መቅረብ አለበት፣
5. በየደረጃው የተቀመጠው ተጨማሪ ዝርዝር የደረጃ መስፈርቶችና የሰው ኃይል ስለ መሟላቱ መረጃ መቅረብና መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

4/ During the renewal, the annual audit report as audited by external auditors and as endorsed by the General Meeting together with the Association's performance report shall be submitted;

5/ Detailed and verified information shall also be submitted for each category of level as meeting the requirements

## 15.<u>የአገልግሎት ክፍያ</u>

በዚህ መመሪያ በአንቀፅ 7 በየደራጀው የኦፐሬተርነት የብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት በመንግሥት የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ መክፈል አለበት፡፡

## <u>15. Service Fee</u>

A Service fee shall be paid, as may be determined by the government, for securing each category of Level stated under Article 7 of this Directive.

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>የአሰራርና የሥነ ምግባር ጉድለት እና የሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች</u>

## <u>Part Five</u>

## <u>Practical and Ethical Violations and Administrative Measures</u>

### 16. <u>የአሰራርና የሥነ ምግባር ጉድለት የቅጣት አወሳሰን</u>

አግባብነት ባለዉ አካል የወጡ ሌሎች ህጎችና ደንቦች ተፈፃሚነታቸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ መመሪያ የተመለከተዉን አጠቃላይ የአሰራር እና ሥነ-ምግባር ጉድለቶችን በመፈጸም ኃላፊነትና ግዴታን በትክክል ባልተወጣ ማንኛዉም የጭነት ትራንስፖርት ኦፕሬተር የሚወሰደዉ አስተዳደራዊ እርምጃ ከዚህ መመሪያ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

### <u>16. Penalty for Practical and Ethical Violation</u>

Without prejudice to the applicability of laws and regulations issued by the competent organ, non-observance by any freight transport operator of the general practical and ethical provisions of this Directive would entail administrative penalties as annexed to this Directive.

## 17.የጭነት ትራንስፖርት ኦፕሬተሮች የቅጣት እርከን

1. በዚህ መመሪያ የተዘረዘሩት የዲስፕሊን ግድፈቶች በተሽከርካሪ ባለንብረቶች፣ አሽከርካሪዎች፣ በማህበር/ድርጅት ሰራተኞች ለሚፈፀሙ የስነ- ምግባር ጉድለቶች ፈቃድ የተሰጠው የጭነት ትራንስፖርት ኦፕሬተር በዚህ መመሪያ የሚጠየቅ ይሆናል፡፡
2. ማንኛዉም የጭነት ትራስፖርት ማኅበር በአባሪ ከተጠቀሱት ጥፋቶች አንዱን ፈፅሞ ከተገኘ፡-

**ለአንደኛ ዕርከን ጥፋት የሚወሰድ አስተዳደራዊ ዕርምጃ፡**

ሀ. ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ የፅሁፍ ማሰጠንቀቂያ ይሰጣል፤

ለ. ለሁለተኛ ጊዜ ከሆነ ከማንኛዉም አገልግሎት ለአንድ ወር ይታገዳል፣

ሐ. ለሶስተኛ ጊዜ ከሆነ የአባላት ጠ/ጉባዔ ተጠርቶ በማህበሩ አመራር ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፣

መ. ከድርጊቱ ሳይታረም በዚሁ ለአራተኛ ጊዜ ከቀጠለ ፈቃዱ እንዲመልስ ይደረጋል፡፡

## 17. Penalty Level for Freight Transport Operators

1/ disciplinary offenses listed in this Directive shall be applicable on owners of vehicles, drivers; for ethical violations committed by employees of associations/companies the licensed freight transport operator shall be accountable based on this Directive;

2/ Any freight transport Association found to have violated any of the offenses stated in the annex:

**Administrative Penalty for first category Offence**

a. Written warning if first time offence;

b. Suspension from any service for one month if second time offence;

c. Termination of the Management through the General Assembly if third time offence;

d. Cancellation of the license if committed for fourth time

**ለሁለተኛ ዕርከን ጥፋት የሚወሰድ አስተዳደራዊ ዕርምጃ፡**

ሀ. ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ ከማንኛዉም አገልግሎት ለአንድ ወር ይታገዳል፣

ለ. ለሁለተኛ ጊዜ ከሆነ የአባላት ጠ/ጉባዔ ተጠርቶ በማህበሩ አመራር ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፣

ሐ. ከድርጊቱ ሳይታረም በዚሁ ለሶስተኛ ጊዜ ከቀጠለ ፈቃዱ እንዲመልስ ይደረጋል፡፡

3. ማንኛዉም የጭነት ትራንስፖርት ድርጅት በአባሪ ከተጠቀሱት ጥፋቶች አንዱን ፈፅሞ ከተገኘ፡-

**ለአንደኛ ዕርከን ጥፋት የሚወሰድ አስተዳደራዊ ዕርምጃ**

ሀ. ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ የፅሁፍ ማሰጠንቀቂያ ይሰጣል፤

ለ. ለሁለተኛ ጊዜ ከሆነ ከማንኛዉም አገልግሎት ለሶስት ወር ይታገዳል፣

ሐ. ለሶስተኛ ጊዜ ከሆነ ከማንኛዉም አገልግሎት ለስድስት ወር ይታገዳል፣

መ. ከድርጊቱ ሳይታረም በዚሁ ለአራተኛ ጊዜ ከቀጠለ የምዝገባ ፈቃዱ ይሰረዛል

.

**Administrative Penalty for second category Offence**

a. Suspension from any service for one month if first time offence;
b. Termination of the Management through the General Assembly if second time offense;
c. Cancellation of the license if committed for third time.

3/ Any freight transport company found to have violated any of the offences stated in the annex:

**Administrative Penalty for first category Offence**

a. Written warning if first time offence;
b. Suspension from any service for three month if second time offence;
c. Suspension from any service for six months if third time offence;
d. Cancellation of the license if committed for fourth time.

**ለሁለተኛ ዕርከን ጥፋት የሚወሰድ አስተዳደራዊ ዕርምጃ**

ሀ. ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ ከማንኛዉም አገልግሎት ለሶስት ወር ይታገዳል፣

ለ. ለሁለተኛ ጊዜ ከሆነ ከማንኛዉም አገልግሎት ለስድስት ወር ይታገዳል፣

ሐ. ከድርጊቱ ሳይታረም በዚሁ ለሶስተኛ ጊዜ ከቀጠለ የምዝገባ ፈቃዱ ይሰረዛል

4. ማንኛዉም የጭነት መኪና አሽከርካሪ በአባሪ ከተጠቀሱት ጥፋቶች አንዱን ፈፅሞ ከተገኘ፡-

**ለአንደኛ ዕርከን ጥፋት የሚወሰድ አስተዳደራዊ ዕርምጃ**

ሀ. ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ የፅሁፍ/የቃል ማሰጠንቀቂያ ይሰጣል፤

ለ. ለሁለተኛ ጊዜ ከሆነ ከማንኛዉም አገልግሎት ለአንድ ወር ይታገዳል፣

ሐ. ለሶስተኛ ጊዜ ከሆነ ከማንኛዉም አገልግሎት ለስድስት ወር ይታገዳል፣

መ. ከድርጊቱ ሳይታረም በዚሁ ለአራተኛ ጊዜ ከማንኛዉም አገልግሎት ለአንድ ዓመት ይታገዳል፣

**ለሁለተኛ የጥፋት ዕርከን የሚወሰድ አስተዳደራዊ ዕርምጃ**

ሀ. ለመጀመሪያ ጊዜ ከሆነ ከማንኛዉም አገልግሎት ለስድት ወር ይታገዳል፣

**Administrative Penalty for second category Offence**

a. Suspension from any service for three months if first time offence;
b. Suspension from any service for six months if second time offence;
c. Cancellation of the license if committed for third time.

4/ Any driver of freight transport vehicles found to have committed any of the offences stated in the annex:

**Administrative Penalty for First category Offence**

a. Written/oral warning if first time offence;
b. Suspension from any service for one month if second time offence;
c. Suspension from any service for six months if third time offence;
d. Suspension from any service for one year if committed for fourth time.

**Administrative Penalty for second category Offence**

a. Suspension from any service for six months if first time offence;

ለ. ለሁለተኛ ጊዜ ከሆነ ከማንኛዉም አገልግሎት ለአንድ ዓመት ይታገዳል፤

b. Suspension from any service for one year if second time offense;

**18.<u>የጥፋት ሪኮርድ አያያዝና ቅጣት</u>**

ማንኛውም የጥፋት ሪከርድ መመሪያውን ባወጣው አካል ተመዝግቦ ይያዛል፤ የጥፋት ሪከርዱም ለሁለት (2) ተከታታይ ዓመታት የሚያገለግል ሲሆን የጥፋት ሪከርዱም የማብቅያ ጊዜ በመንግሥት የበጀት ዓመት መሠረት ይሆናል፡፡ ነገር ግን በወንጀል ተሳትፎ የተገኘ ከሆነ የጥፋ ሪከርዱ ለቀጣይ አራት (4) ዓመታት ተመዝግቦ የሚቆይ ይሆናል፡፡

**<u>18. Penalty Record and Fine</u>**

Any penalty record shall be kept by the issuing authority of this Directive; the record shall be kept for two /2/ consecutive years and ends in alignment with the government’s fiscal year. Where, however, the offence involve a criminal act the record shall be kept for four /4/ years.

**<u>ክፍል ስድስት</u>**

**<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>**

**<u>Part Six</u>**

**<u>Miscellaneous Provisions</u>**

**19. <u>የተቀናጀ የጭነት ትራንስፖርት ኦፕሬተር አስተዳደር ስርዓት</u>**

1. አደራጅ አካሉ የኦፕሬተሮችን ዝርዝር መረጃ በተቀናጀ የጭነት ትራንስፖርት ኦፕሬተር አስተዳደር ስርዓት ላይ አደራጅቶ ይይዛል፡፡
2. ማንኛውም ኦፕሬተር በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8 እና አንቀጽ 13 ላይ የተገለፁትን መስፈርቶች በማሟላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በተገለጸው ኦፕሬተር አስተዳደር ስርዓት ላይ ማስመዝገብ አለበት፡፡

**<u>19. Integrated Freight Transport Operator Management System</u>**

1. The organizing body shall organize the details of operators on an integrated freight operator management system.
2. Every operator shall comply with the requirements set out in Article 8 and Article 13 of this Directive and register in the opereator management system described in sub - article 1 of this Article.

## 20.ስለ ቁጥጥር

ይህን መመሪያ የሚያስፈጽመው የአደራጅ አካሉ ይሆናል፡፡

## 21.የቁጥጥር ሠራተኛ ተግባርና ኃለፊነት

1. ለቁጥጥር የተሠማራው ሠራተኛ ራሱን የሚገልጽ መታወቂያ እና ታፔላ ይዞ መገኘት አለበት፣
2. በቁጥጥር ሂደት ጥፋት ተፈጽሞ ከተገኘ ተቆጣጣሪው (የአደራጅ አካሉ ተወካይ) ወዲያውኑ የጥፋት ሪፖርት ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ማቅረብ አለበት፡፡
3. አሽከርካሪዎችን በተመለከተ በቁጥጥር ሂደት ጥፋት ተፈጽሞ ከተገኘ ተቆጣጣሪው ወዲያውኑ የክስ ወረቀት በመሙላት ዋናውን ለተከሣሹ አስፈርሞ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡
4. አስተዳደራዊ እርምጃዎች በተመለከተ በሌሎች ህጎች የተቀመጡት ቅጣቶች እንደተጠበቁ ይሆናል፡፡

## 20. Enforcement

The Organizing body shall be responsible for the implementation of this Directive.

## 21. Duties and Responsibilities of Enforcement Officers

1/ an Enforcement Officer on duty shall possess Identification Card and Badge to this effect;

2/ where offence is found to have been committed by the Enforcement Office he shall immediately report the offence together with his recommendation;

3/ where during duty an offence is found to have been committed by drivers, the Enforcement Officer shall immediately issue a traffic charge and hand over the original charge receipt to the driver;

4/ Administrative measures contained in other laws remain effective.

## 22.የቅሬታ አቀራረብ ስነ ስርዓት

1. በመመሪያው መሰረት አገልግሎት ያላገኘ ማንኛውም ኦፕሬተር ወይም ቅሬታ ያለው አካል መጀመሪያ ቅሬታውን አገልግሎቱን ለሚሰጠው የአደራጅ አካሉ ዳይሬክቶሬት ማቅረብ አለበት፣
2. ጉዳዩ የሚመለከተው ዳይሬክቶሬት የቀረበውን ቅሬታ የማይፈታለት ከሆነ ቅሬታውን ለዘርፉ ም/ዋና ዳይሬክተር/ኮሚሽነር ማቅረብ ይኖርበታል፤
3. የዘርፉ ም/ዋና ዳይሬክተር/ኮሚሽነር የቀረበውን ቅሬታ ካልፈታ ለአደራጅ አካሉ ዋና ዳይሬክተር/ኮሚሽነር ማቅረብ ይኖርበታል፤
4. የቀረበውን ቅሬታ ተቋሙ መፍታት ካልቻለ ቅሬታውን ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ማቅረብ ይችላል፡፡ ለቅሬታው በሚኒስቴሩ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

## 22. Grievance Procedure

1/ any operator or grieving body with a complaint relating to the services based in the Directive shall lodge his complaint to the Directorate delivering the service in the organizing body;

2/ where the complaint hasn't been addressed by the Directorate, he shall lodge his complaint to the Deputy Director or Deputy Commissioner leading the section;

3/ where the complaint hasn't been resolved by the Deputy Director or Deputy Commissioner, he shall lodge the appeal to the Director General or Commissioner of the organizing body;

4/ where the authority hasn't resolved the complaint an appeal may be lodged to the Ministry of Transport. The decision of the Ministry shall be final.

## 23.የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1. ቀደም ሲል የነበሩ ማህበራት ይህ መመሪያ ተፈጻሚ ከሆነበት ዕለት ጀምሮ ባሉት ሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ሀብትና ንብረታቸውን በውጪ ኦዲተሮች ማስመርመርና በጠቅላላ ጉባኤ ማጸደቅ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ በዚህ መመሪያ መሰረት እንደገና መመዝገብ አለባቸው፡፡
2. ቀደም ሲል የነበሩ ድርጅቶች ይህ መመሪያ ተፈጻሚ ከሆነበት ዕለት ጀምሮ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ በዚህ መመሪያ መሰረት እንደገና መመዝገብ አለባቸው፡፡

## 24.የተሻሩ መመሪያዎች

1. የድንበር ተሻጋሪ የጭነት ትራንስፖርት ኦፕሬተሮች የአደረጃጀት የደረጃ መስፈርትና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ መመሪያ ቁጥር 1/2006 ሙሉ ለሙሉ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡
2. የአገር ውስጥ የጭነት ትራንስፖርት ኦፕሬተሮች የአደረጃጀት የደረጃ መስፈርትና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ መመሪያ ቁጥር 2/2006 ሙሉ ለሙሉ በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## 25. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህን መመሪያ አደራጅ አካሉ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሊያሻሽለው ወይም ሊሽረው ይችላል፡፡

## 23. Transitional Provisions

1/ All active Associations prior to the coming into force of this Directive shall have their assets and properties audited by external auditors and endorsed by their General Assembly within three months and shall be re-registered in accordance with this Directive within six months from the effective date of this Directive.

2/ All active Operators prior to the coming into force of this Directive shall be re-registered in accordance with this Directive within six months from the effective date of this Directive.

## 24. Repealed Directives

1/ Organizational and Grading Requirement of Cross-Border Freight Operators Directive No. 1/2006 is hereby repealed.

2/ Organizational and Grading Requirement of In-land Freight Transport Operators Directive No. 2/2006 is hereby repealed.

## 25. Amendment

The organizing body may amend or repeal this Directive where appropriate.

**26.የመመሪያው ተፈፃሚነት**

ይህ መመሪያ 16/02/2013 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አብዲሣ ያደታ**
**የፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን**
**ዋና ዳይሬክተር**

**26. Effective Date**

This Directive shall come in to effect on 26/10/2020.e

**ABDISSA YADETA**

**DIRECTOR GENERAL**

**FEDERAL TRANSPORT AUTHORITY**

# ሠንጠረዥ ሀ

## የአስተዳደራዊ እርምጃዎች አወሳሰድ፣ እና አጠቃላይ የአሰራር እና ሥነ-ምግባር ጉድለቶች

### 1. አንደኛ ዕርከን የጥፋት ዝርዝር

| ተ.ቁ | አንደኛ ዕርከን የጥፋት አይነቶች ዝርዝር |
|---|---|
| 1 | ኦፕሬተሩ የአባል ተሽከርካሪዎችን መረጃ በተሟላ ሁኔታ አደራጅቶ አለመያዝ እና ሲጠየቅ ትክክለኛ መረጃ ወቅቱን ጠብቆ አለመስጠት |
| 2 | ማንኛውም የጭነት ትራንስፖርት ማኅበር፣ ድርጅት ወይም ግለሰብ የብቃት ማረጋገጫ ፈቃዱ እና ትክክለኛ ስያሜአቸውን በቢሮ ዉስጥ ለዕይታ በሚያመች መልኩ አስቀምጦ አለመገኘት፣ ሲጠየቅም ለማሳየት ፈቃደኛ አለመሆን፣ |
| 3 | ከተደራጀበት ማህበር መዉጫ ሳይዝ በሕገ-ወጥ መልኩ ጭነት ማጓጓዝ |
| 4 | የአባል ተሽከርካሪዎችን ማህበሩ በጨረታ ካሸነፉ ወይም በ sub contract በውል ከወሰዱት ጭነት ዉጪ እንዲጭኑ መዉጫ መስጠት፣ |
| 5 | ከተገልጋዮች ለሚቀርቡ ቅሬታና አቤቱታዎች ተገቢ ምላሽ አለመስጠትና ለዚሁ የአሰራር ሥርዓት እንዲኖር አለማድረግ፣ |
| 6 | የማህበሩ ወይም የድርጅቱ ተሽከርካሪ የጭነት ማዘዣ ሳይኖረዉ ወደ ወደብ እንዲሄድ ማድረግ፣(የተላከ መሆኑ በማስረጃ ሲረጋጋጥ) |
| 7 | የባለስልጣኑ መስሪያ ቤት ባወጣዉ የደረጃ መስፈርት መሰረት የማህበሩን ወይም የድርጅቱን ስም እና አርማ የያዘ የጐን ስቲከር በተሽከርካሪዎች በሁለቱም ጎን አለመለጠፍ |
| 8 | በማንኛውም ጊዜ መመሪያው ላይ የተቀመጡ መሟላት የሚገባቸዉን መስፈርቶች አሟልቶ አለመገኘት፣ |
| 9 | ያለ ውል ጭነት ማጓጓዝ |
| 10 | ኦፕሬተሩ ለአደራጅ አካሉ ያሳወቀውን አድራሻ ሲቀይር በመመሪያዉ በተቀመጠዉ የጊዜ ገደብ ዉስጥ አለማሳወቅ |

## Schedule A

## Administrative Measures and General Operational and Ethical Violations

**1. First Category of offence**

| No | Types of First Category of offence |
|---|---|
| 1 | The operator does not fully organize the information of the member vehicles and does not provide accurate and seasonal information at request. |
| 2 | Any freight transport association, enterprise or sole proprietor not to put exact name in the office in convenient manner to view, or not to show competency license at request |
| 3 | Transport the cargo illegal way without having exit paper from the organized association. |
| 4 | Giving exits for member vehicles to be loaded outside of the auction cargo won by the association or sub-contract. |
| 5 | Not to give appropriate response to grievances and petitions submitted by customers and not to create operational network thereof. |
| 6 | Making to move the vehicle of association or enterprise to port without exit paper. |
| 7 | Not to stick on both sides of vehicles the sicker taking the name and logo in accordance with the standards of level issued by the authority. |
| 8 | Not fulfill at any time the requirements stated under the Directive and that are appropriate to be fulfilled. |
| 9 | Transport cargo without a contract. |
| 10 | Not to announce within the time limit stated under the Directive when the Operator changes its address announced to the |

| | |
|---|---|
| | organizing body. |

## 2. ሁለተኛ ዕርከን የጥፋት ዝርዝር

| ተ.ቁ | ሁለተኛ ዕርከን ዝርዝር የጥፋት አይነቶች |
|---|---|
| 1 | የማኀበሩን ወይም የድርጅቱን ዓርማ፣ ማኀተምና ሙሉ አድራሻ የያዘ የጭነት ማዘዣ፣ መከታተያ /Logbook/ እና ሌሎች የኦፐሬሽን ሰነዶችን አለማዘጋጀትና ሥራ ላይ አለማዋል፣ |
| 2 | ኦፐሬተሩ አዲስ ስራ አስኪያጅ ሲቀጥር ወይም በስራ ላይ የነበረዉ ሲለቁ ወይም ሲሰናበት ለባለስልጣኑ መስሪያ ቤት አለማሳወቅ፤ |
| 3 | የተሟላ የኦፐሬሽን መረጃ ያላደራጀና ሲጠየቅም በተሟላ መልኩ የተጣራ መረጃ በአግባቡና ወቅቱን ጠብቆ መስጠት ካልቻለ ወይም ፈቃደኛ ካልሆነ እንዲሁም ወርሐዊ ሪፖርት በወቅቱ ያለመላክ፤ |
| 4 | የተሸከርካሪዎች እንቅስቃሴና ፍጥነት መቆጣጣሪያ መሳሪያ ብልሽት ገጥሞት እንዲያስተካክል የጊዜ ገደብ ተሰቶት ያላስተካከለ ኦፐሬተር |
| 5 | የተሽከርካሪዎችን እቅንስቃሴ ለመቆጣጠር የሚረዳ ስርዓት በራሱም ሆነ በሶስተኛ ወገን የሚተዳደር የተሽከርካሪ መቆጣጠሪያ ስርዓት ያልዘረጋ ኦፐሬተር |
| 6 | የማህበሩን የተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ መረጃ አደራጅ አካሉ ማግኘት በሚያስችል መልኩ የተዘረጋውን ሰርዓት 24 ሰዓት ክፍት ያላደረገ ኦፐሬተር |
| 7 | ለእያንዳንዱ ተሽከርካሪ የተመደበ አሽከርካሪ እና ከባለንብረቱ ጋር የተፈፀመ የስራ ቅጥር ውልና የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያላቀረበ ማህበር |
| 8 | ከህጋዊ የአገልግሎት አሰጣጥ ሰነድ ውጭ ያለ ማህበሩ ስምሪት ፈቃድ ሐሰተኛ ሰነድ አሽከርካሪው እንዲጠቀምና እንዲሰራ ማድረግ ወይም አለመቆጣጠር፣ ወይም በዚህ ድርጊት ራሱ ፈጻሚ ሆኖ መገኘት፣ |
| 9 | የመንገድ ትራፊክ ደኅንነት ዩኒት በማቋቋም አደጋን ለመቀነስ በሚደረገው ሀገራዊ ጥረት ተሣታፊ አለመሆን፣ |

| | |
|---|---|
| 10 | የማህበሩ የቦርድ አመራር አባላት ተሽከርካሪያቸውን በአደጋ፣ በሽያጭ፣ ከደረጃ በመውረድ ወይም በብልሽት ምክንያት ከአገልግሎት ዉጪ ሲሆኑ ሌላ ተሽከርካሪ ከሌላቸዉ በስተቀር አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ በመጥራት በምትካቸዉ ማሟያ ምርጫ አለማድረግ፤ |
| 11 | አስፈላጊዉን ቅድመ ሁኔታ በማሟላት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ወቅቱን ጠብቆ አለማደስ፤ |
| 12 | በአደራጅ አካሉ እንዳይሠሩ የታገዱ ሠራተኞችን ቀጥሮ ሲያሰራ መገኘት፤ |
| 13 | የጭነት ትራንስፖርት የአደረጃጀት ብቃት ማረጋገጫና የአፈፃፀም መመሪያ፣ ሞዴል መተዳደሪያ ደንብ ሙሉ ለሙሉ ሥራ ላይ እንዲውሉ አለማድረግ፣ |
| 14 | ከባለስልጣኑ መስሪያ ቤት የአባልነት መመዝገቢያ ደብዳቤ ሳይደርሰዉ ባለንብረቶችን በአባልነት መመዝገብ ወይም ለተሽከርካሪዎች የመውጫ ሰነድ መስጠት፣ |
| 15 | በባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ በወጣዉ የደረጃ መስፈርት መሰረት ደረጃዉን የማይመጥን ተሽከርካሪ እንዲሰራ ማደረግ፣ |
| 16 | በወደብ ላይ የጭነት ክምችት በሚፈጠርበት ጊዜ በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በሚሰጠዉ ኮታ ድልድል መሰረት አለመስራት ወይም ለመስራት ፈቃደኛ አለመሆን |
| 17 | የሌላ ማህበር/ድርጅት አርማና ስቲከር በተሽከርካሪዎች ላይ ለጥፎ መገኘት |
| 18 | ህገ ወጥ የሰዎች ዝዉዉር ተባባሪ በመሆን ስደተኞችን ደብቆ ማጓጓዝ፣ እና ያልተፈቀዱ ህገ ወጥ ጭነቶችን ማጓጓዝ |
| 19 | የኮንትሮባንድ እቃ ማጓጓዝ፣ ህገ-ወጥ የጦር መሳሪያ ይዞ መገኘት ወይም ወደ ጎረቤት ሀገር ይዞ መግባት |
| 20 | የጫነዉን ጭነት በጥራት ወይም በብዛት ማጓደል ወይም በጫነዉ ጭነት ላይ ባዕድ ነገር በመቀላቀል የዕቃዉን ጥራት እንዲጓደል ማደረግ፣ |
| 21 | የማህበሩ/ድርጅቱ አሽከርካሪዎች ወይም ወኪሎች በአድማ ላይ መተባበር ወይም ለአድማ ሌሎችን በማነሳሳት ተግባር ላይ መሳተፍ |
| 22 | ማህበራት በሞዴል መተዳደሪያ ደንቡ መሰረት በየሁለት (2) ዓመቱ የአደራጁ አካል ተወካይ በተገኘበት ጠቅላላ ጉባዔ አለመጥራት እና በውጭ ኦዲተር ሂሳቡን አለማስመርመር፤ |

| | |
|---|---|
| 23 | የብቃት ማረጋገጫ የሌለውን ተሽከርካሪ እንዲሰራ ያደረገ ወይም ያሠራ፣ |
| 24 | በድርጅት/ማህበር ወይም ባለንብረትና አሽከርካሪ መካከል የሥራ ውል ሳይኖር ማሰራት ወይም ህገ ወጥ አሽከርካሪን ቀጥሮ ማሰራት |
| 25 | በንግድ ያልተመዘገበ(ግል ንግድ) ተሽከርካሪ ወደ ንግድ ሥራ ወይም ወደ ኪራይ ማሠማራት፣ |

**2. Second Category of offence**

| No | Types of Second Category of offence |
|---|---|
| 1 | Not organizing and putting in to practice Logbook and other operational documents taking the logo, seal and full address of the association or enterprise. |
| 2 | Not to announce to the Authority when the Operator hire new manager, or when the manager resins the job, or when the manager fired by the Operator. |
| 3 | Not to organize and when using in exhaustive manner, when the Operator cannot give appropriate full operational information and not submit seasonal monthly report. |
| 4 | An Operator that not makes adjustment within a given time limit when the speed limit of the vehicle is defective. |
| 5 | An Operator that cannot unroll a system helping to control the movement of the vehicles administered by its own or by third party. |
| 6 | An Operator that do not make open 24 hours the unrolled system taking the information of vehicles of the association at a visible place in orderly manner. |
| 7 | An association which do not submit deployed driver to each vehicle, employment contract made with the owner of the property and Driving Qualification License. |

| | |
|---|---|
| 8 | Making the driver to use forged document out of the document of trip schedules of legal delivery of services or not controlling or being the doer of it. |
| 9 | Not participate in the national effort to reduce danger by establishing road traffic safety unit. |
| 10 | Not calling urgent meeting and making supplementary election by the board of association when their vehicles damaged, soled, degraded from the level, unless they have a vehicle. |
| 11 | Not renew license of competence at the appropriate time by fulfilling the necessary requirements. |
| 12 | Employing the workers suspended by the Organizing Body. |
| 13 | Not making fully applicable the Commercial truck Operators' Organizational Qualification Certification and Excursion Directive and Model statutes and |
| 14 | Registering owners of the property in the membership or giving the exit paper to the vehicles without receiving from the Authority membership registration letter. |
| 15 | Making to do the vehicles not fulfilled the standards of level issued by the Authority. |
| 16 | Not doing or not being voluntary to do in accordance with the quota given by the Authority when the cargo is Dumped at Port. |
| 17 | Sticking on vehicles the logo and sticker of other associations or enterprises. |
| 18 | Collaborating in unlawful moving of persons and migrants and transporting prohibited cargos in the hidden way. |
| 19 | Transporting contraband goods, holding unlawful army weapons or holding and entering in to neighbor countries. |
| 20 | Decreasing the quality and quality of cargos or mixing up defective and extraneous goods together with the loaded cargo. |
| 21 | Collaborating in conspiracy the drivers or agents of associations or enterprises or participating in instigation of others. |
| 22 | Not calling general meeting in each second year in accordance with model statutes of the association and not auditing by the outside auditor. |
| 23 | Making to do the vehicle not having license of competence. |

| | |
|---|---|
| 24 | Making to do without employment contract between enterprise/association or the owner of vehicle and deriver. |
| 25 | Making to do non-registered vehicles commercial activities or rent. |

# አባሪ 1

## በደረጃ መስፈርቱ መመሪያ መሠረት መረጃዉ ስለመሟላቱና ትክክል ስለመሆኑ የተሰጠ ማረጋገጫ

እኔ/እኛ________________ አድራሻ ___________ክ/ከተማ__________ወረዳ____________

ልዩ መጠሪያ____________ የቤትቁጥር____________የስልክ ቁጥር___________

ለድርጅታችን ☐ ለማኅበራችን ☐ ለደረጃ_________ምድብ_____የወጣውን መሥፈርት የምናሟላ ስለሆነ ደረጃ እንዲሰጠን እንጠይቃለን፡፡ ደረጃው ቢሰጠን

1. በመሥፈርቱ መሠረት የተሽከርካሪውንም ሆነ ለተቋሙ የተሰጠውን ደረጃ በተሟላ ሁኔታ በመጠበቅ አገልግሎት እንሰጣለን፡፡
2. በንግድ ህጉ በየብስ ዕቃ የማጓጓዝ ሥራ ለመደንገግ የወጣውን አዋጅ ቁጥር 547/99 እና የትራንስፖርት አዋጅ 468/97 ሕግና ደንብ አውቀንና ተገንዝበን ሥነ-ምግባር ያለው አገልግሎት እንሰጣለን፡፡
3. በባለሥልጣኑ መ/ቤት የሚጠየቁ አስፈላጊ መረጃዎችን እንሰጣለን፣ በተቋማችን የአደረጃጀትና ሌሎች ለውጦች ሲኖሩ ወዲያውኑ ለትራንስፖርት ባለሥልጣን እናሳውቃለን፡፡

4. የሥራ አፈፃፀማችን በትራንስፖርት ባለሥልጣንና በሌሎች ገለልተኛ አካላት በየጊዜው እየተገመገመ የሚሰጠንን ደረጃ እንቀበላለን፡፡

5. ከዚህ ደብዳቤ ጋር በአባሪነት የተያያዙት/የቀረቡት መረጃዎች ሁሉ ትክክል ስለመሆናቸዉ ከዚህ በታች ባለዉ ፊርማና ማህተም እናረጋግጣለን

ሥም፡- ________________________________

ፊርማ፡- ________________________________

ማህተም

**Annex- 1**

**<u>Proof of completeness and accuracy of the information in accordance with the standards</u>**

I / We -------------------------- Address-----------------Sub-City-------------------------- Woreda --------------

Special name--------------------------House No.------------- Tel.No.----------------

Ask for our organization ☐ our association ☐ for a Level ☐ as we meet the standards set. If the Level is given:

1. We provide services in full compliance with the requirements of the vehicle and the level given to the institution.

2. We are aware of the laws and regulations of Proclamation No. 547/99 enacted to regulate the transportation of Goods by land and the Transport Proclamation No. 468/97.

3. We will provide the necessary information required by the Authority, and we will immediately inform the Transport Authority when there are any organizational and other changes in our institution.

4. We accept the Level we get on the evaluation of our performance by the Transport Authority and other independent bodies on a regular basis.

5. We certify that all information attached/presented to this letter is correct with the signature and stamp below.

Name: -----------------------------------------

Signature: -------------------------------------

Seal

## አባሪ 2

## የተቋሙ ንብረት የሆኑ ወይም በተቋሙ የተደራጁ የጭነት ተሽከርካሪዎች ዝርዝር

## /በተቋሙ የሚሞላ/

| የባለንብረት ስም | የመኪና የሰሌዳ ቁጥር | የሞተር ቁጥር | የመኪና ሻንሲ ቁጥር | የተሳቢ ሰሌዳ ቁጥር | የተሳቢ ሻንሲ ቁጥር | የስራት ዘመን | | የመጫን አቅም በኩንታል | | ጠቅላላ ድምር በኩንታል | የፍሊት ማኔጅመንት መሣሪያ የተገጠመላቸው ተሽከርካሪዎች ብዛት | የአገልግሎት ዓይነት | ተጨማሪ መግጫ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | የመኪና | የተሳቢ | የመኪና | የተሳቢ | | | | |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | | | |

*ማሳሰቢያ፡የአገልግሎት ዓይነት ሎቤድ፣ ሀይቤድ፣ ቁም እንስሳት ማጓጓዝ፣ በልክ ጭነት ማጓጓዝ ወዘተ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡*

**Annex- 2**

| Vehicle owner Name | Vehicle Plate Number | Engine number | Vehicle chassis Number | Trailer Plate Number | Trailer chassis Number | Manufacturing Year | | Load capacity in quintal | | Toatal Sum in quintal | Number of vehicle equipped with fleet management | Service Type | Additional Description |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | Vehicle | Trailer | Vehicle | Trailer | | | | |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | | | | | |

**<u>Note:</u> The type of service may include lobby, Hybed, Transport of livestock, freight transport, etc.**

**አባሪ3**

# የኦፐሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሠርተፊኬት

**በትራንስፖርት ሚኒስቴር**
**የፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን**

**የኦፐሬተር የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሠርተፊኬት**
**የደረጃ---**

ቁጥር_______________
ቀን _______________

_____________________የጭነት ትራንስፖርት ድርጅት/ማህበር በወጣው የደረጃ መስፈርት መሠረት ተመዝኖ የደረጃ---ብቃት ማረጋገጫ ምዝገባ ፈቃድ እንዲሰጠው ባቀረበው ጥያቄ መሠረት፡-

## 1. የተሽከርካሪዎች ብዛትና የማንሳት አቅም

| የተሽከርካዎች ዝርዝር ሁኔታ | | | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የተሽከርካሪ ብዛት | የአገልግሎት ዘመን | 30 ቶን እና በላይ | ከ20 - 30ቶን | ከ3.5- 20ቶን | 7ቶን እና በላይ | |
| | ከ 0-15 | | | | | |
| | ከ 0 - 25 | | | | | |
| | ከ 0-10 | | | | | |
| | ከ 25 በላይ | | | | | |
| የማንሳት አቅም/ቶን | | | | | | |

## 2. ለደረጃው የሚፈለገው የሰው ሃይል፣የቢሮ አደረጃጀትና ሌሎች መስፈርቶች የተሟላ ነው፡፡

በመሆኑም መስፈርቱን ያሟላ ስለሆነ ይህ የደረጃ ------- የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ተሰቶታል፡፡ በዚህ የብቃት ደረጃ የሚሰጥ አገልግሎት_____________________________________________
_____________________________________________

ከሠላምታ ጋር

ፊርማ -------------------
ቀን ----------------------

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ለ---------------- ታድሷል<br>ፊርማ -------------------<br>ቀን ----------------------- | | ለ---------------- ታድሷል<br>ፊርማ -------------------<br>ቀን ----------------------- | | ለ---------------- ታድሷል<br>ፊርማ -------------------<br>ቀን ----------------------- | | ለ---------------- ታድሷል<br>ፊርማ -------------------<br>ቀን ----------------------- |
| የደ.ቁጥር ----------------- | | የደረሰኝ.ቁ ---------------- | | የደ.ቁ ---------------------- | | የደረ.ቁጥር --------------- |

*ማሣሰቢያ፡- ይህ የብቃት ደረጃ ማረጋገጫ ፈቃድ በየዓመቱ መታደስ አለበት፡፡*

**Annex- 3**

# Operator Competency License Certificate

**By the Ministry of Transport**

**Federal Transportation Authority**

**Operator Certification License Certificate**

**Rank --------**

**Number:__________________________**

**Date፡____________________________**

**________________________________________Freight Transport Enterprise evaluated according to the standards, According to the application for a Level---------- Operator competency Licence :**

1. **Number of vehicles and lifting capacity**

| **Details of Vehicle** | | | | | | **Total** |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **Number of Vehicle** | **Service Year** | **30 Ton and above** | **20-30 Ton** | **3.5-20 Ton** | **7 Ton and above** | |
| | **0-15** | | | | | |
| | **0-25** | | | | | |
| | **Above 25** | | | | | |
| **Lifting capacity/Ton/** | | | | | | |

2. The Required manpower, office organization and other requirements are met.

**Therefore, this Level-------- of Freight Transport Operator Competency is licensed. Service Provided under this Operator Competency Licence is:_____________________**

With regards

Signature_____________________________________ Date_____________________

| **Renewed for__________** | | **Renewed for__________** | | **Renewed for__________** | | **Renewed for__________** |
|---|---|---|---|---|---|---|
| Signature_____<br>Date_________ | | Signature_____<br>Date_________ | | Signature_____<br>Date_________ | | Signature___________<br>Date_______________ |
| Receipt No. _________ | | Receipt No. _________ | | Receipt No. _________ | | Receipt No. _________ |

Notice: This Competency Licence shall be renewed annually.

# አባሪ 4

## ሀ. ለማህበራት የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ መስፈርት፣

| ደረጃ | የአባላት ወይም ተሸከርካሪ ብዛት | የተሸከርካሪ ዕድሜ | የመጫን አቅም | በአንድ ጊዜ ጭነት የማንሳት አቅም |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 150 | ከ 15 ዓመት ያልበለጠ | ከ 30 ቶን ያላነሰ | 4500 ቶን |
| 2 | 100 | ከ 15 ዓመት ያልበለጠ | ከ 30 ቶን ያላነሰ | 3000 ቶን |
| 3 | 75 | ከ 15 ዓመት ያልበለጠ | ከ 30 ቶን ያላነሰ | 2250 ቶን |
| 4 | 50 | ያለ ገደብ | ከ 7 ቶን ያላነሰ | 350 ቶን |

## ለ. ለአክሲዮን ማህበር የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ መስፈርት፣

| ደረጃ | የአባላት ወይም ተሸከርካሪ ብዛት | የተሸከርካሪ ዕድሜ | የመጫን አቅም | በአንድ ጊዜ ጭነት የማንሳት አቅም |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 50 | ከ 15 ዓመት ያልበለጠ | ከ 30 ቶን ያላነሰ | 1500 ቶን |
| 2 | 30 | ከ 15 ዓመት ያልበለጠ | ከ 30 ቶን ያላነሰ | 900 ቶን |
| 3 | 20 | ከ 15 ዓመት ያልበለጠ | ከ 30 ቶን ያላነሰ | 600 ቶን |
| 4 | 10 | ከ 10 ዓመት ያልበለጠ | ከ 3.5 - 20 ቶን ያላነሰ | 35 ቶን |
| 5 | 5 | ያለ ገደብ | ከ 7 ቶን ያላነሰ | 35 ቶን |

## ሐ. ኃ/የተ/የግ/ማህበር የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ መስፈርት፤

| ደረጃ | የአባላት ወይም ተሽከርካሪ ብዛት | የተሽከርካሪ ዕድሜ | የመጫን አቅም | በአንድ ጊዜ ጭነት የማንሳት አቅም |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 30 | ከ 15 ዓመት ያልበለጠ | ከ 30 ቶን ያላነሰ | 900 ቶን |
| 2 | 20 | ከ 15 ዓመት ያልበለጠ | ከ 30 ቶን ያላነሰ | 600 ቶን |
| 3 | 10 | ከ 15 ዓመት ያልበለጠ | ከ 30 ቶን ያላነሰ | 300 ቶን |
| 4 | 10 | ከ 10 ዓመት ያልበለጠ | ከ 3.5 - 20 ቶን ያላነሰ | 35 ቶን |
| 5 | 5 | ያለ ገደብ | ከ 7 ቶን ያላነሰ | 35 ቶን |

## መ. ለግል ትራንስፖርት የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ መስፈርት፤

| ደረጃ | የአባላት ወይም ተሽከርካሪ ብዛት | የተሽከርካሪ ዕድሜ | የመጫን አቅም | በአንድ ጊዜ ጭነት የማንሳት አቅም |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 25 | ከ 15 ዓመት ያልበለጠ | ከ 30 ቶን ያላነሰ | 750 ቶን |
| 2 | 15 | ከ 15 ዓመት ያልበለጠ | ከ 30 ቶን ያላነሰ | 450 ቶን |
| 3 | 5 | ከ 15 ዓመት ያልበለጠ | ከ 30 ቶን ያላነሰ | 150 ቶን |
| 4 | 5 | ከ 10 ዓመት ያልበለጠ | ከ 3.5 - 20 ቶን ያላነሰ | 21 ቶን |
| 5 | 5 | ያለ ገደብ | ከ 7 ቶን ያላነሰ | 35 ቶን |

**Annex- 4 Operators Competency Requirement**

| 1. Operator competency requirement for Associations | | | | |
|---|---|---|---|---|
| Level | number of members or vehicles | Vehicle Age | Loading Capacity | Lifting capacity At a time |
| 1 | 150 | Not exceeding 15 years | Not less than 30 Ton | 4500 Ton |
| 2 | 100 | Not exceeding 15 years | Not less than 30 Ton | 3000 Ton |
| 3 | 75 | Not exceeding 15 years | Not less than 30 Ton | 2250 Ton |
| 4 | 50 | unlimited | Not less than 7 Ton | 350 Ton |
| **2. Operator competency requirement for a Share company** | | | | |
| Level | number of members or vehicles | Vehicle Age | Loading Capacity | Lifting capacity At a time |
| 1 | 50 | Not exceeding 15 years | Not less than 30 Ton | 1500 Ton |
| 2 | 30 | Not exceeding 15 years | Not less than 30 Ton | 900 Ton |
| 3 | 20 | Not exceeding 15 years | Not less than 30 Ton | 600 Ton |
| 4. | 10 | Not exceeding 10 years | 3.5- Not less than 20 Ton | 35 Ton |
| 5 | 5 | unlimited | Not less than 7 Ton | 35 Ton |
| **3. Operator competency requirement for a Private Limited company** | | | | |
| Level | number of members or vehicles | Vehicle Age | Loading Capacity | Lifting capacity At a time |
| 1 | 30 | Not exceeding 15 years | Not less than 30 Ton | 900 Ton |
| 2 | 20 | Not exceeding 15 years | Not less than 30 Ton | 600 Ton |
| 3 | 10 | Not exceeding 15 years | Not less than 30 Ton | 300 Ton |
| 4. | 10 | Not exceeding 10 years | 3.5- Not less than 20 Ton | 35 Ton |
| 5 | 5 | unlimited | Not less than 7 Ton | 35 Ton |
| **4. Operator competency requirement for a Sole proprietorship** | | | | |
| Level | number of members or vehicles | Vehicle Age | Loading Capacity | Lifting capacity At a time |
| 1 | 25 | Not exceeding 15 years | Not less than 30 Ton | 750 Ton |
| 2 | 15 | Not exceeding 15 years | Not less than 30 Ton | 450 Ton |
| 3 | 5 | Not exceeding 15 years | Not less than 30 Ton | 150 Ton |
| 4. | 5 | Not exceeding 10 years | 3.5- Not less than 20 Ton | 21 Ton |
| 5 | 5 | unlimited | Not less than 7 Ton | 35 Ton |